# ኩልና ተኮላ

t.me/BooksandYou

ተኮላ የተባለ ሰው አፍቅሬ በትዳር መኖር ከጀመርኩ አሁን ሰማንያ ሰባት ነው አይደል? አዎ አንድ አመት ተኩል አለፈኝ:: በዚህ......ማለት......በቃ......ከእሱ ጋር አንድ ቤት ውስጥ ሚስቱ ሆኜ በመኖሬ ደስተኛ ነኝ:: አንዳንድ ሰዎች በማያገባቸው መግባት የሚወዱ ወይም የማናቀፍ ጉጉታቸው ወሰን የሌለው *ለምን ተኮላን አገባሽው?* ይላሉ:: ብቀርባቸውም ባልቀርባቸውም ነው:: ያጠያይቃል እንዴ? ካገባሁት አገባሁት ነው:: ድርቅና በሉት ወይም ፈጣጣነት

በሉት ብቻ ግራ ያጋቡኛል፣ ምን ግራ ያጋቡኛል፣ ይደብሩኛል ልበል እንጂ:: ሁልጊዜ የምመልሰው *ስለወደድኩት* ብዬ ነው:: ፊታቸውን አዙረው ወይም ለማንሾካሾክ እንዲመቻቸው ከእኔ ፈቀቅ ብለው ከሚመስላቸው ጋር (ከአሽሙዋጣጩ ጋር፣ ከአናቃፊ ጋር፣ የውሸት ተጠራጣሪ ጋር፣ የሀቁን ቀናኢ ጋር) *ነው ሰንዴ?* አንደሚሉ እገምታለሁ:: የሕልውናን ትርጉም በሚያበላሽ ቋንቋ እንደ እነሱው በልቼና ጠጥቼ ያደኩ መሆኔን በሚያስቅ ስልት ይረሳሉ:: የሚጠይቁኝ ከእሱ ጋር መኖሬ አከራካሪ አንዲሆን ስለሚሹ ነው:: የጠራ ሲያዩ ለማደፍረስ ስለሚቃጡ (ዓይኖቻቸው ቀልተው)፣ አለ አይደለ ካፈቀርኩት ሰው ጋር በመኖሬም ደደብ ቅናት ጨምድዶአቸው:: ሌላ ምን ሊሆን ነው ታዲያ? ደጋግመው ሲጠይቁኝ ዝባዝንኬ ሳላበዛ ዝባዝንኬም ስለማልወድ *ተኮላን ያልወደድሽ ማን ነበረሽ?* የሚል እራሳቸውንም የሚጨምር መልሴን እወረውራለሁ:: የከፈቱአቸውን አፎቻቸውን ሳያስጠጡ ይዘጋሉ::

ቤተሰቦቼ በዕድሜ እኔን እጅግ የሚበልጠኝ ተኮላን በማግባቴ ይበሳጫሉ:: አያስገርመኝም:: ታዲያ ዘመኑ ነፃ አድርጎን ይሄው የወደድነውና የወደደን ወንድ ቤት ዘው ብለን እንገባለንና ከጥንት ባህል ሲቃረንባቸው ምን ያድርጉ? ሌላ ምን ሊሆን ነው ታዲያ? ካልተጠለፉ፣ ወይም ዘመድ፣ ወዳጅና ቤተሰብ ካልፈቀደላቸው የማያገቡበት ዘመን ስለተወለዱና ሰለአደጉ አልፈርድባቸውም:: የምፈርደው በዞረባቸው ባሁኖቹ 'ወጣት ነን' በሚሉ የመንፈስ አጁዛዎች ነው:: በአደባባይ ስለነፃነት የሚነሰንሱት ፍልስፍናቸው በልቦናቸው ክፋትና ድንቁርና ሲሰረዝ፣ ቃላተ-ዲሞክራሲያቸው በልጋጋቸው ውሃ ሲታጠብና ከቁጩ ብራናቸው ላይ ሲለቅ፣ ይኼው እንዲህ ያጋጥመኛል:: ዕጣዬ በዕድሜ የገፋ ሰው ላይ ቢጥለኝም፣ ምንአለበት ፍቅር ክንድ ላይ ነው::

ግን ደሞ *አልተመቻችሁኝም* ብትሏቸው ማረፍ አባታቸውን ገሏልና፣ (ወይም ዘር ማንዘራቸውን) የዘጉትን አፋቸውን መልሰው መላልሰው እየከፈቱ (ሃፍረተ-ቢስነት የለመደባቸው)፣ የነገር መንገድ ትንሽ ቀያይሰው፣ በፈጣጣ አማርኛ 'እሱ እኮ ሴት መያዝ ይችልበታል' ይላሉ:: ይሄ አባባል ግልፅ አይደለም:: የበሰልኩ ነፃ ልጅ ስለሆንኩ 'መያዝ' የተባለው ቃል ሲያልፍ አይነካኝም:: እወደዳለሁ እንጂ አልያዝም:: ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ተኮላ ያለውን ችሎታ አልደብቅም:: *መያዝ* ማፍቀርን ከተካ

ጠማማው የዘመኑ አተረጓጎም እንጂ የእኔ እንዳልሆነ ይቆጠርልኝ ዘንድ ያለትህትና እጠይቃለሁ::

መዋሸት ማንን ይጠቅማል? ራሴን ለመከላከል ብዬ ትንሽ ሳላጠቃልል አልቀርም:: በራሴ ጉዳይ አክራሪ ብሆን አውደልዳዮች ምን አገባቸው? ትንሽ ግን አለበት:: ከመያዙ ማለቴ ነው:: ማፍቀሩ ግን ዋናው ነው:: መናዘዜ አይደለም:: ሰሙኝ የእኔ እንኮዬ?

ልቤን ጠልቀው ያላዩ ከሶስት ጠማማ *አብረሽ ምቺው* አቅጣጫዎች ሊገመግሙኝና ሊፈርዱብኝ ይሞክራሉ:: ከራሳቸው እምነት፣ ከሌሎች እምነት እና ከራሴና ከተኮላ ትንንሽ ድርጊቶች:: ይሄ የትም ቦታ ዕውቀት ማግኛ መንገድ ነው:: ማለቴ ደንብ ነው:: ሃሳብና እሱን የሚያጅበው ፍርድ ከሰማይ አይወርድም:: ያው ካደገሽበትና ከተወለድሽበት ነው:: የመለኮት ጉዳይ አስመሰለው ብዙ አይራቀቁ:: አናውቀዋለን ማለቴ ነው::

ጠንካራው መረጃ ግን ከእኔ አኗኗርና እምነት የሚመጣው ነው:: አይደል? ከእሱ የሚታየው ነው:: አይደል? *'እሆ'* ይበሉኝ:: ባይስማሙም *'እሆ* ደግ ነው:: እንደሚሉት ከተቃቃሩ ላይቀር ተግባብቶ ይሻላል::

እኔ የሚታይብኝ ያው ድርጊቴና ለተኮላ ስላለኝ ፍቅር በተገኘው አጋጣሚ ሲለፈልፍ የሚደመጠው የማላቆመው አፌ ነው ('አይ ጊዜ' ብለው ሰዎች እንደሚያማርሩ፣ 'አይ አፌ' አልልም):: ችሎበት ልቤን ጠልቆ ላላየ ወይም ገብቶ እንዲፈትሽኝ ያልፈቀድኩለት፣ የተኮላን ስም በቁልምጫ ስጠራ የሰማ፣ ልብሱን በትኩረት አጥቤ ሳሰጣ ያየ፣ (በተለይ በክራቫት የሚለብሳቸው የሚያሳዝኑኝ ሸሚዞቹ)፣ ባገኘሁት አጋጣሚ እንደ ድመት እየታከኩ ሳቅፈው ለተመለከተ፣ የከፋው ሲመስለኝ በእሱ ምትክ ስነፈርቅ ለታዘበ፣ ወይም እንደ ሁሉን አወቅ ደራሲ ወይም እንደ አምላክ አልጋችን ላይ የምንሆነውን የሚያይ(አልጋ ውስጥ በገባን ቁጥር የደረቱን ጉተና በአፌ እየነጨሁ ያሳመምኩትን ያየ፣ ወይም ረዥም ቁመናውን እንደዛፍ ስወጣውና ሰወርደው ያጤነ) ከእሱ ሌላ ማንንም መውደጃ ልብ እንደሌለኝ ይገባዋል:: ይሄ ሁሉ እውነት ነው::

አዩ:: ገና አስራ ሁለተኛ ክፍል የጨረስኩ ነኝ:: እኔም ቤተሰቦቼም ያለንበት የኢኮኖሚ ሁኔታ አሳሳቢ ሆኗል:: ኑሮው ሳያቋርጥ ችግር ውስጥ እየከተተን ነው:: አባቴ ባለ ባችለር ዲግሪ ቢሆንም አራት ቤተሰቦቹን ማሳደሪያ አቅም እያጠረው መጥቷል::

በዘመኑ ጣጣ ኩራቴና ፍርሃቴ ይዞኝ እንጂ፣ እንደ ሌሎች የእኔ እድሜ እኩያ ኮረዶች ሽርሙጥና መግባቴ አይቀርም ነበር፡፡ እንዳንዳንድ ልጃገረዶች በነጠላ ተሸፋፍኜ ቀን ከወጣለት ሽማግሌ ጋር ማደር ነበረብኝ፡፡ ሃብት ባለው መናጥ እንደ ማለት፡፡

አዎ፤ ቤተሰቦቼ የሚበሉት የምግብ መጠንና አይነት፣ የሚለብሱት ልብስ ጥራት አጠያያቂ እየሆነ ከመጣ ከርሟል፡፡ ታናሽ እህቴ ትቀምላለች፡፡ ይሄ ማለት ባለዲግሪው አባቴ አድርጎት የማያውቀውን በቀላሉ ተባይ ማሳደግ ጀምሯል፡፡ ታዲያ ምን ማድረግ አለብኝ? ዛሬ ዛሬ በእኔ እድሜና እውቀት ስራ ማግኘት ከባድ ነው፡፡ የሕልም ላም እንደ ማለብ ነው፡፡ ሕልሙም ከታለመ ነው እንግዲህ፡፡ (ለምን እናልማለን? አጎንብሰን ብንፈትሽ ብንፈትሽ ላሞቻችን የሁዋላ እግሮች መሃል ግት አላየንም)

ይሄን የቤተሰቤን ችግር ሳነሳ *ለገንዘቡ አገባሁት* ልትል ዳር ዳር አለች፣ *የጠረጠርነው ልክ ነው* እንዳይሉ የግምትዎን መሳሳት ላስታውስዎ እፈልጋለሁ፡፡ ከላይ ያልኩትን ሁሉ ስል ተኮላን አልወደውም ማለቴ አይደለም፡፡ ብልጣ ብልጥ እንዳልባል ለማረም መቻኮሌም አይደለም፡፡ የእውነት እወደዋለሁ፡፡ በማያውቁት፣ በደንብ ባልገባዎ ነገር ጥልቅ ማለት ባህልዎ ሳይሆን አይቀርም፡፡ የምን ‘ሳይሆን አይቀርም’ ነው፡፡ ‘ነው’ ልበል እንጂ፡፡

ሁለቱ ተቃራኒ የመሰሉት ነገሮች አንድ ላይ መምጣት አይችሉም ያለው ማነው? በመጀመሪያስ ተቃራኒ ያደረጋቸው ማነው? ኢትየጵያ እንድትጠፋ የሚመኙ አንዳንድ ሚኒስቴሮች አሉ እኮ፡፡ ሚንስቴር ደሞ ችሎታ የለውም፣ እውቀት የለውም ማለት አይደለም፡፡ ታዲያ ይሄ ሲሆን አንዳንድ ተመልካች፣ (የዋሁን ማለቴ ነው) ትርጎማ ላይ ዞር ይልበታል እና መሳሳቱ አይቀርም፡፡ ሁለቱ የህልውናዬ ፈርጆች ውስጥ ስላለሁ አንዳንድ ቅን ድርጊቶቼ ወደ ማልፈልገውና ወደ ምፈልገው ትርጉም ተርጉዋሚዎቹን ሳይፈቅዱ ይወስዷቸዋል፡፡ ለምሳሌ በዛ አድርጌ አስቤዛ ከገዛሁ ‘ለዘመዶችሽ ልትወስጂ ነው’ እንዳልባል እሰጋለሁ፡፡ *ሆኗል* ማለቴ ሳይሆን ሊተረጎም ይችላል፡፡ አንዳንዴ በየሁለት ወሩ በርበሬና ሽሮ ነገር ለራሴ ሰፋ አድርጌ ሳስፈጭ ለእነሱም ቆንጥሬ መውሰዴ አይቀርም፡፡ ይሄም ብዙ አይደለም፡፡ እነሱ እንኩዋን በስጋና በዕድገቴ የሚቀርቡኝ ከእስዎ የሃሳብ ወንዝ ቀድተዋል መሰል፣ ከሃብታም የዘየድኩ ስለሚመስላቸው አንዳንዴ ከሽሮና ከበርበሬ በላይ ድጎማ ይጠብቃሉ፡፡ በእኔ ትዳር በግ ያምራቸዋል፡፡

ዶሮ በየወሩ ይቁዋምጣሉ:: ካላደረኩት ‘አይ ያንቺስ ትዳር’ ብለው ማሽሙዋጠጣቸው አይቀርም:: ባይሉኝም፣ አንዳንዴ ችግራቸውን ተናግረው (‘ምን የዘንድሮ ኑሮ......ምኑ ከምን......’) ብሌናቸው ስትጠብ አያለሁ (የሚጠብ ብሌን አያሳይዎ):: ታዝቤም ተበሳጭቼም የሚሉኝን ተብዬና ተገምቼ ምን ይደረጋል አልፋቸዋለሁ::
የእርስዎን ይተውት፤ በአጭሩ የዘመዶቻችን ጆሮዎችና ልቡናዎች እንደ ባዕድ የሚያደርጋቸው ስንቴ ነው?
ተኮላ በራሱ ባይሆንም አባትና እናቱ እጅግም ባይሆን ሃብታም ናቸው:: በአኗኗሬም ከመውደድ እንጂ ከካሽ ጉዳይ እንዳሌለኝ እንዲረዳ ራሴን ማስዋቢያ ውድ ነገር አልገዛም:: ቀሚስ ስለሚወድ ሁልጊዜ ደስ የሚለውን ቀሚስ እገዛለሁ:: የምሰራለትን ምግቤን ስለሚወድ ምግብ ሰሪያችን ነኝ:: ትርፍርፍ ነገር ማድረግ ብታማ ነድ ቀለም ባላቸው ብዙ የውስጥ ሱሪዎቼና ፒጃማዎች ነው:: እሱም የትዝታችን ነው:: ቤታችን አምስት ክፍል አለው: ከፊል ብሎኬት ከፊል ሽክላ የሆነ የድሮ ቤት ነው:: ባይገርምዎ በመጋረጃ አቅም ልዋጭ አልገዛሁም:: እንዲገዛም አላሳሰብኩትም ወይም አልገፋፋሁትም:: ያው ስንጋባ ሶስት ጉዋደኞቼ ሃና፣ ትሩፋትና ምስል (ዛሬ ባህሬይን ሄደዋል) ከእተጌ እደጥበብ በስጦታ የገዙልኝ ነው:: እንደምፈልገው ባያምርም ‘ወዳጆቼን አስታውስበታለሁ’ እያልኩ እዋሽዋለሁ:: የማጠናባት፣ የማነብባትና የምኳኳልባት የራሴ ትንሽ ክፍል አለችኝ:: ሙዚቃ ስለምወድ እሱን ላለማስቸገር ከራሴ ቤት ያመጣሁዋትን አሮጌ ካሴት ማጫወቻ እጠቀማለሁ:: ሌላ ‘ሌተስት ማጫወቻ ግዛልኝ’ ብዬ አልገፋፋሁትም:: ‘መዘነጥ ማንን ገደለ?’ ብሎ ሳሎኑን በዘመናዊ ቁሳቁስ ሞልቶታል:: የማልክደው የግቢያችንን ውብነት ነው:: በአበባ ያሸበረቀች ናት:: ለዚህ ገንዘብ አውጥቼአለሁ: ለደቅዳቂ፣ ለቆፋሪ፣ ዘር አምጪና ዘሪ፣ ለኮትኳች:: ጠዋት ጠዋት እሱ ከአልጋው ተነስቶ ቁርሱን ሊቆርስ ተጣጥቦ እስኪጠብቀኝ፣ በአበቦቹ መሃል ስመላለስ ደስ ይለኛል:: አበቦቹ ውስጤ የበቀሉ ይመስለኛል:: ግን የሁሉንም ተክሎች ስም አላውቅም፣ ባውቅም በእንግሊዘኛ ነው:: ሙሉ ቀን እረፍት በምንሆንበት እሁድ እዛ ተንሸራሽሬ ሲበቃኝ ተኮላ እተኛበት ሄጄ ጎኑ ስጋደም ከውስጤ ለፍቅረኛዬና ለባሌ የሚፈሰው ቅን ማር ነው:: ብዙ ጊዜ እሁድ ከሰአት በሁዋላ ሲኒማ ወይም ቲያትር ካልገባን ወይ እውጭ እንብላ

ብሎ የሆነ ሬስቶራንት ካልሄድን ዳማ እንጫወታለን። ከዳማው ሰሌዳ ጀርባ በወፍራም የደበዘዘ ጥቁር ማርከር፡

*ሀፒ በርዝ ደይ[1] ተኮላ*
*1978 ቤላ*

የሚል አለው። ለምን ልጅቷ በዚህ አይነት ቀለም በዚህ አይነት መጠን ስሟን እንደፃፈች አይገባኝም። አንዳንዴ በቅናት ስሜት ሳይሆን በቀልድ ‘እስኪ ቤላን አምጣትና እንጫወት’ እለዋለሁ። ዳማ ጨዋታ ሲሰለቸን በቪዲዮ የተቀረፁ የአማርኛ ኮሜዲ ፊልሞችን እናያለን። የተኮላን ደረትና በጥብስ የሞቀ ሆድ ተደግፌ፣ ጋቢ እግሮቼ ላይ ጣል አድርጌ፣ እቅፍ አደርጎኝ እጋደማለሁ። እንዲህ ሲሆን ብዙም በማያስቀው መሳቄ የተለመደ ነው። ከመሃል በጋቢ ስር ይዳብሰኛል፣ ይኮረኩረኛል። ‘ተው እባክህ ልስማበት’ እያልኩ ውሃ እንደምትጠጣ ዶሮ እያንጋጠጥኩ እስመዋለሁ። አገሪቷ ላይ መሬት መንቀጥቀጥ ደርሶ ሶስት ሚሊዮን ህዝብ አለቀ ቢባል የምሰማ አይመስለኝም።
‘ፍቅር እኮ ድንቁርና ነው’ ቢሉ አልታዘብዎትም። ግን ካላወቁ፣ ካልገባዎ፣ ሊገባዎም ካልፈለጉ፣ እኔ የምነግርዎትን በትንሹ እንኩዋን ካልኖሩ ዝም ይበሉልኝ። የምር ዝም ይበሉ።
ተክዬ ትምህርቱ ከአስራ ሁለተኛ አላለፈም። በዛ ዕድሜው ደህና ትምህርት አልቀሰመም፣ ኮሌጅ አልደረሰም ብዬ አላፍርበትም። እሱም አያፍርም። የሃብቱ ብቃት እኔን አይነት ዕድሜዋ ሃያ የሆነች ወጣት ድሮት የለም? ተኮላ አንዳንዴ የተማሩ አንጀባ ሲያደርጉበት ቢሰሙትም ባይሰሙትም ‘የሁሉ ነገር መጨረሻው እኮ ካሽ ነው’ ይላል። ሲል ግን እኔን ሂሳብ ውስጥ ከቶ አይደለም። እኔ ጅማ ለገንዘቡ እንዳልመጣሁ ያምናል። ጥሩ ነጋዴ የመሆን ስጦታ በተፈጥሮው እንዳለው አምናለሁ። አፍ ስላለው ነው ንግድ ይሆንለታል ያልኩት። ምክንያቱም ንግድ ማለት መሸወድ መቻል ስለሚመስለኝ ነው። አጣመው አይተርጉሙት፤ ይሄ ፀባይ ካለው እኔን ሸውዶኛል ማለቴ አይደለም። ምን ለመገመት አለፉዎት?
እኔንስ ምን ብዙ አስወራኝ? ብቻ ሁሉ ነገር ተደምሮና ተቀንሶ ተኮላ ለእኔ ትክክለኛ ሰው ነው።
ሲጀመር ይፈራኝ ነበር። *ለምን አይሉም?*። ልጅ ናት እያለ። *መቼ ጀምረሽ ብትወጂው ነው?* የሚለውን ጥያቄ ባልመልሰው ይሻላል። ይሄን በሚመለከት ነገር ባሳጥር ደግ ሳይሆን አይቀርም። የወደድኩት ትላልቅ

ልጃገረዶች ስለ እሱ በአድናቆት ሲያወሩ ሰምቼ ነው:: በልጅነት ጆሮዬ እንደለቃቀምኩት የምትንቀው ሴት አላጋጠመኝም::

ተኮላ እንግዲህ ከሰው ተግባቢ ስለሆነ በሰፈር ለቅሶና ሰርግ አይጠፋም:: ይሄንን አውቃለሁ:: ማንም ያኔ በዛ እድሜዬ በሌላ ነገር ስለማይጠረጥረኝ እሱን ፍለጋ ለቅሶ እደርሳለሁ:: ያልተጠራሁበት ሰርግ እሄዳለሁ:: እሱ እተቀመጠበት አካባቢ እቀመጣለሁ:: በፍቅሩ እየነደደኩ ዕድሜዬ አስራ ሰባት ሞላ::

በአንድ አመት ተኩል ጊዜ ውስጥ መሰለኝ ተማሮ *የሆነ ይሁን* አይነት አወጣኝ:: *ማስመረር* ስል ማንም ላይገባው ይችላል:: *ምን ፈለገች ከእኔ?* ብሎ ይቀጥረኝና ሻይና ምሳ ጋብዞኝ ይሸኘኛል:: እያበላኝ እያጠጣኝ *ምን ፈለገች ከእኔ?* እያለ እየቀረበ ይርቀኛል:: የተሰላቸ ዕለት(የቆረጠ ብል ይሻላል) ሆነ:: ከዚያ ቀን በሁዋላ አልተወኝም:: ከታዛቢ አይኖች ለመሸሽ ብዙ ጊዜ ተደብቀን ወጣን:: አይዘለቅምና ሁሌ መደበቅ፣ አደባባይ መታየት ጀመርን:: ወሬው ዘነበ:: ወሬው ጎረፈ:: ያው እላይ እርስዎ የሚሉኝ አይነት፡ ‘*ልጁን ጠበሰ*’ ‘*አባቷን ጠበሰች*’:: ለመሆኑ ምን አገባቸው? የዕውነት ተገርመው ነው ወይስ በማዳነቅ ወሬውን አስፋፍተው እኔና ተክሽ አፍረን ፍቅራችንን በይሉኝታ እንድንተወው ነው? ቀበሌዬን ያልጠረጠርኩ (ያውም ኡራኤልን) ማንን ልጠርጥር? ከሰፈሬ ሴቶች ልሻማውና ከታላላቆቼ ልስተካከል ቢቻል ልበልጥ ላይ ታች ተንቀልቅዬ ‘ልቀምሰው’ የሄድኩት ልጅ ሚስቱ ሆኜ አረፍኩት:: ገና በደንብ ሳንተዋወቅና አንሶላ ሳንጋፈፍ ያሳየኝ የነበረው ቸልታ፣ ንቀትና ትዕቢት ጠፉ:: ተኬ ለሰለሰ:: አላደረኩትም እንጂ በዛን ሰሞን ‘*እግሬን ሳም*’ ብለው ‘*ከየት ጋ ልጀምር የእኔ አመቤት? ከቁርጭምጭምትሽ ላይ ወይስ ከጥፍርሽ?*’ ሂሂሂ እንደሚለኝ አውቃለሁ:: ጉራ አይደለም::

ልቡ ገባሁ:: እዛም ጎዝጉዤ ተቀመጥኩ:: ይሄን ስናገር እሱን ‘ከላይ አስከ ታች እናውቀዋለን’ የሚሉ ሁሉ አላመኑም:: (የእኛ ሰፈር አዋቂ ይገርመኛል፣ ላባ አይቶ ‘አሞራ አየሁ’ የሚል፣ ጅና አይቶ ‘አንበሳ አየሁ’ የሚል፣ ጠብታ ውሃ አይቶ ‘ዶፍ በዚህ አልፎ ነበር’ የሚል፣ ኩታ ያዘወተረ ሁሉ አባቱ ሽማኔ የሚመስለው አይነት ነው:: እነዚህን ዓይነቶች ፖለቲከኛ አያርግብዎ) የተኮላ ልብ ማንንም አልያዘማ:: ፌሽታ አባቱ ፍንደቃ እናቱ:: ያገኘውን ሴት መጉስጎስ ሆቢው:: ያውም የተደነቀበት:: ‘ሽርሜ ስለሆንሽ ሽርሜ ወደድሽ’ የሚሉኝ አይጠፉም::

የሚያደንቁት ዛሬም አያፍሩም ‘እናውቀዋለን’ ብለው ሲተርቱ:: ብህትውናን እያሳየን፣ የደጀ ሰላም ሰልፍ እያሞቅን፣ መስጊድ እየተደረደርን የመሳሰለ የምንደብቀው ትልልቅ ባለጌነታችንንና ባለጌዎችን ነው:: እዚህ የተሰራሪዎች ጎርፍ እንኮዬ ሆይ እግሬን አላስገባሁም:: የተቀናበረ ይሁን ያልተቀናበረ ወጥመድ አልገባሁም:: የዚያ አይነት መንገድ አልመረጥኩም:: ሁለታችንም ፍቅር ነን:: ‘ተክዬ’ ስለው፣ ለምን ልዋሸዎ አፌን እንገር እንገር ይለኛል:: ተኮላን *በእጇ አስገባሁት* ስል የእውነቴን ነው:: ግን ከእሱ እውቀት ውጭ አይደለም:: *በእጅ ማስገባት* ስል እሱን አሻንጉሊት አድርጌ እንዳልሆነ ይወቁት:: ይሄ ይሄ ወደ ትክክለኛው ምክንያት መጠጋት ሲሳናቸው፣ ወይም የጉዳዩ ባለቤት ስለአይደሉና ምክንያቱ ሲሰወርባቸው፣ ወይ ወሬአቸው በመረጃ አልደገፍ ሲላቸው፣ ወይ በቅናት ሲብሰለሰሉ፣ ወይ መበለጣቸው ሲቆረቁራቸው ወዘተ ወዘተ……በቀላሉ ይታመናል ብለው የገመቱት ራሳቸውን አዋቂ የሚያስመስላቸው ልብወለድ ሃሳብ ነው:: አይገርመኝም ይታመናሉ:: አይገርመኝም ቢታመኑ:: አማኞቹ ጅሎች ወይም የዋሆች ናቸው:: ጅልንና የዋህን የምከላከልበት አቅም የለኝም::

አንዳንዶቹ እንደሚሉት ልጅነቴ ማርኮት ነው:: ይሄ በማንም የተበላ ምክንያት ነው:: ልጅነቴ አዎ ይማርካል:: ደሞ ልጅነቴ እኔ አይደለሁም እንዴ? ልጅነቴን ከሌላ አገር ገዝቼ እንደ ልብስ አለበስኩት:: ተፈጣሪነቴም እዚህ ነው:: ሲስመኝ አፉ ላይ አበባ አበባ ብለው የእዚህ አገር ስለሆንኩ ነው:: ቀይ ዳማ ቆዳዬን እየላሰ የጨውን መአዛ ቢወድ እሱም የእኔ ነው:: የብድር አይደሉም:: የዩኤን፣ የዩሮ ወይም የአሜሪካ አይደሉም:: ጥርሶቼ ቢነጡ ራሴ ፍቄአቸው ወይ ዘረ ነጭ ስለሆንኩ ነው:: በጀርባዬ ተንጋልዬ መርፌና ክር ስንሆን ደስታ የገፋው ዕንባዬ የጠረገው ኩሌን አጎንብሶ ቢልስ እሱም የእኔ ስለሆነ ነው:: ብልጠታቸው አያልቅምና ከቡና አንቃራሪዎች ተወልደው በእነሱም እጅ ያደጉ ነገረኞች ስለሆኑ እኔን ከልጅነቴ ሊነጥሉኝ ሁለት ጎን ያበጁልኛል:: ልጅነት ሲሉ ቁንጅናዬም እንዲዘነጋ ፈልገው ነው:: ልክ በእድሜዬ ብቻ ተኮላ እንደ መረጠኝ ሁሉ:: እንደ እነሱ እንደነሱ አባባል (ምናልባትም እንደ እርስዎ) ሶስት ሰዎች አልሆንም? ልጅነቴ፣ ቁንጅናዬና እኔ:: እትዬ አይግረምዎ:: ከእስዎም፣ ከእሷም ከአንቺም ከአንተም ከሁላችንም ጋር አብሮ ያደገ በህብረት የምናጨበጭብለት ልማድ ስለሆነ

እየዘነጋነው ነው:: ማለት ጠማማነትን:: ከራሱ የተጣላ ወለወልዳ ህብረተሰብ እንዲህ ያዘባርቀናል ግን የትም አይደርስ:: ትንንሽ በመሳሰለ ነገር እየተፋፋቅን እየተናናቅን አብረን የምናልቅ:: ሲበለሻሽብን በሰይጣን ወይ በእዝጌር ልናመሃኝ:: ሁለቱም የፈረደባቸው::

በቁንጅና አላምንም:: ቁንጅና እንደተመልካቹ ነው ካላችሁ እንዴት *ቆንጆ ነኝ* ብዬ እርስዎን ላሳምን እችላለሁ? አዎ ደህና ነኝ:: አላስከፋም:: ተኮላ ለምን ያቺን ትንሽ ጡቴን እንደ ሞሳ ይለጠፍባታል? ከወተት ወተት፣ ከውሃ ውሃ የላት:: ጫፎቻቸው ሲከሩ ሲያይ ለምን የተኮላ አይኖች ዕንባ ያቀራሉ? እግሮቼን ሲያነሳ የጭኖቼን ውስጥ ለምን እያማጠ ይስማቸዋል? ለምን ማታ ማታ በሆዴ አስተኝቶ የቂጤን ጉንጮች በሁለት እጆቹ ይዞ ክብነታቸውን ያደንቃል? ከሌሎች ሴቶች በውበቴ ብለይ አይደለ? ለምንድነው ካለረዠም ቀሚስና ሱሪ በተቀር አጭር ቀሚስ ለብሰሽ እንዳላይሽ የሚለኝ? የቆዳዬ ልስላሴ፣ ቅርጼና እግሮቼ እንዳይታዩ አይደለ:: እንደሚቀና ስለማውቅ (ግን ሳልነግረው)፣ በረዠም ቀሚስ እንደ ገርዳሜ በየአደባባዩ እንጀላጀላለሁ:: ለእሱ ፍቅር የከፈልኩት አንዱ መስዋዕትነት ነው:: ሌሎች እሱ የተዋቸው ሴቶች እርስዎንም ጨምሮ አንድ ጡትና ሶስት ከንፈሮች ነበራችሁ እንዴ? እባክዎ እንኮዬ ይሄ *ውበት እንደ ተመልካቹ ነው* የሚባለውን ተረት ይርሱ:: ማንጉዋጠጤ አይደለም:: የማንም ፉንጋ፣ ቦርጫምና ለምቦጫም *ውበት እንደተመልካቹ ነው* ብላ ራሷን ብትደልል ፎሪ ወጣሽ እንላታለን:: አለማማር አለ ሲወለዱ:: ለመማረክ ያልተፈጠሩ አሉ:: ጉራ አይደለም:: *ውስጤ ውብ ነው* ብለው ራስዎን አይደልሉ:: ያገሬን ወንድ፣ *ከአገርህ ዞማ ከአገርህ አላማ የቱን ትመርጣለህ* ቢሉት፣ ዞማ ይዞ ዋሽንግተን ይገባል:: የሰማሁት ሳይሆን ያየሁት ነው:: ፍልስፍና አላበዛም እውነቱ ይሄ ነው::

*የሰፈሩ ሴት አልቀረውም* እየተባለ ተኮላ እኔን ሚስት ማድረጉ እስከ አሁን ከዘረዘርኩት ሁሉ የበለጠ ያልገባኝ ብዙ ብዙ ፍልስፍና አለው::

በዚህም ሰበብ አንዳንድ ሰፋፊ ቁም ነገሮች ተምሬአለሁ:: አንደኛ የአገራችን ሰው ወሬኛ እንደሆነ:: ሴት በሉ ወንድ:: ሁለተኛ ተኮላ ባልኖረው አኗኗሩ ማለት *ያላወጣት ሴት የለችም* በሚባለው በመመዘኑ የተበደለ መሰለኝ፣ ወይ ትናንት ይሄን ፀባዩን እንደ እርፍና ቆጥረው ከፍ ከፍ ያደረጉት ዛሬ ሊጠልፉት አስበው እንደ ሆነ እንጃ:: ከፍ ከፍ ነው ወይስ ለየት ለየት ነው?

የአገሬ ልጅ ነኝና ምሳሴ ከአፈር የተሰራ፣ ከእኔ ቀድሞ ሌላ ሴት ባለመግሰሱ (እሱ እንደ ነገረኝ ግን ላምነው የከበደኝ) ቀሽም የሆንኩ መሰለኝ:: ካልተፈለገ ወንድ ጋር የወጣሁ መሰለኝ:: ሽርሙጥና በቅናት ተሸፋፍና ትመጣለች:: የክፍት አፎች አገር አልታወጀም እንጂ ያው አንድ ክልል ነው:: እዛ ያልተሰበሰበ አይነት ሽግን የለም:: ይሄን በሚመለከት የመጀመሪያ ትምህርቴን አገኘሁ:: ፍቅር ቦርቃቃ አይደለም:: የአንድ ሰው ሁለንተናነት ነው:: ተኮላን የወደደ ተኮሊስት ነው:: እኔን የወደደ ጅማ ወርቂስት ነው:: ጀሚስት ይሻላል?

እንዳንድ ልምዶች ያሉ ይመስለኛል ስለአለም አጠቃለው የሚነግሩን:: ብዙ አይደሉም:: አለ አይደለ በጣም የምታምኑት ሰው ድንገት ሲከዳችሁ፣ *‘ለካ……አለም እንዲህ ነው እንዴ?’* እንደምትሉት:: ግን የእኔ ሰፋ አለ:: በልጅ አይኔ ወደ እርስዎ ብቻ እያየሁ ‘እንዲህ ናችሁ’ እንዴ? አላልኩም:: እሱንም እንደሚያወሩበት ‘ሴት አውል አይደለሁም’ ብሎ ማስተባበያ ቢነግረኝም፣ ቢናዘዝም፣ በመጠነኛ ትዝብት ግን በልቤ *እንዲህ ዋሾ ነህ እንዴ?* አልኩት:: ለጥቂት ሳምንታት ራሴውኑ ያሳፈረኝ ንቀት እሱ ላይ አድሮብኝ ነበር:: በጉጉት ውስጤ ሲገባ ፍቅር አልመሰል፣ ንፁህ ሴት በማግኘቱ ብቻ የተደሰተ መሰለኝ:: እንዲህ እንደሚወደኝ እያየሁ በሰዎች ርዕዮተ አለም አሱን መመዘን ማለቴ እንደ እርስዎ ማሰብ ማለት የእሱን ይዞታ በእርስዎ መረጃ ላይ ተመርኩዤ መሰለልና መታዘብ ነበረብኝ? አጎንብሼ ባልሄድም ይሄ የአህያነት ምልክት መሰለኝ:: ለጥቂት ቀናት ራሴኑ እየታዘብኩ ሰላጣዬን/ሰርዶዬን ነጭቼ የምሴን አናፋሁ:: ታዲያ ከአህያ ምን ይጠበቃል? የአምባሰል ቅኝት?

ይሄው ቅድም ያልኩዎትን ልድገምልዎ፡ በጣም ስለሚወደኝ *እግሬን ሳምልኝ* ብለው ያውም ሳልታጠብ *ከየት ልጀምር፡ ከጣት ወይስ ከቁርጭምጭሚትሽ?* ብሎ ማጣሪያ እንደሚጠይቀኝ አውቃለሁ:: ታዲያ ለምን አልወደው?

ግን፡

ግን ግን ግን ከሁለት አመታት በላይ ባስከረኝ ደስታ ውስጥ እንደኖርኩ 1987 ግንቦት ውስጥ በሆነ ባልገባኝ ምክንያት ተለወጠ::

ተክዬን ስወደው በአይኖቼ ስሜቱን ከፊቱና ከሌላ ሁኔታው መረጃ ሰብስቤ ብቻ አይደለም:: ብዙ የማይገባው አይነት መገምገሚያ (ካድሬ ብቻ አይደለም የሚገማገመው) ፈተና አስቀምጬ ነው::

ማድቤት የምሰራው ከሌለኝ ሳሎን ሶፋ ላይ ተጋድሜ ወይ አልጋ ላይ መኝታ ቤት ተኝቼ፣ በር ከፍቶ ሲገባ አይኖቼን እጨፍናለሁ:: (ማድቤት ወጥ እያማሰልኩ ከሆነም ድስቱን እከድንና ማማሰያዬን በቀስታ አስቀምጬ) ከአረማመዱ፣ ሲቀርበኝ ከከበበው አየርና ከተከተለው ጠረን፣ ካንቀላፋሁ ደሞ እንዳይቀሰቅሰኝ አድርጎ በስጋት ጉንጬን ሲስመኝ፣ ከከንፈሮቹ ሙቀትና ልስላሴ፣ ፍቅረኛዬና ባሌ ተኮላ ደህና እንደሆነና እንዳልሆነ ማወቅ እችላለሁ:: ወደ ደረቱ ሲያቀርበኝ ከአስተቃቀፉ ጥብቀት፣ ከአፉ ጠረን (እኔን ካወቀ በሁዋላ ነው ሲጋራ ማጤስ ያቆመው)፣ ከሚታከከኝ ፊቱ ላይ ከሚነሳው ሙቀት፣ ከቆዳው ልስላሴ፣ ከጢሙ ሸከራነት፣ ከአይኖቹ አጨፋፈን፣ በሆነ ዘይቤ እንዳልበታተን በክንዶቹ ሲሰበስበኝ፣ እግሮቼን በሰለጠነ ስልት ከፍ ሲያደርግ፣ የጣቶቹ ወገቤና ጭኔ ላይ የሚያኪያሂዱት ሰገብጋባ አስተራረፍ፣ የውስጥ ሱሪዬን የሚያወልቅበት ዘገምተኛ ስልት፣ ወደ ውስጤ ሲዘምት የሚያደርገው አገፋፍና አተነፋፈስ፣ ፍቅረኛዬና ባሌ የጋራ ሃዲዳችን ላይ አንደሆነ አውቃለሁ:: እንዲህ እንደምመረምረውና መርምሬም እንደምረዳው አያውቅም:: እንደ አንዳንድ ሴቶች በገላቸው ብቻ ሳይሆን በመረጃቸው እንደሚሸረሙጡ ከማንም ዕውቀት ለቃቅሜ መጥቼ ተክዬን አልመዘነኩትም:: ተኮላን የጀመርኩት በአዲስ ሰሌዳ ላይ ነው:: አዲስ ስርአት ባሮጌ መረጃ አይመጣም:: የቲቪያችሁ ጥበብ ወይም የወግ ጠራቂነታችሁ ጠል አልቦረቦረኝም::

መለወጥ የጀመረ የመሰለኝ ሰሞን *ምነው ተኪ? ምነው?* አልኩት (ተክነት፣ ተክዬ፣ ትኩ፣ ትኩነት፣ ትኪ፣ ተት፣ ትት፣ ትዬ፣ ትክ የማልለው ቁልምጫ አልነበረም) የአስር ቁልምጫ[1] ልጅ::

*ምንም* አለኝ:: ይሄም ውሸት መሆኑን ለማወቅ የደቂቃ ሩብ አልወሰደብኝም::

አጠገቤ ተቀምጦ ብዙ ብዙ የሚጫወተው (የረባውንም ያልረባውንም) ሰውዬ ፈዘዘብኝ:: ‘ምንም’ ብሎኝ ፍዝዝ ያለ ሳቅ ሳቀ:: ተኮላ ሞቅ ያለ ሳቂ ነው:: ተኮላ የአራዳ ምሳሌ ነው:: ከጨዋታና ከሳቅ ውጭ ምንም አይፈልግም:: በቴሌቭዥን የሆነ ፖለቲካ

---

[1] *ተክነት*--ከእኔ ራቅ ያለ ቦታ ከአለ (ለምሳሌ እኔ አትክልት ቦታ እሱ ሳሎን ካለ)፣ *ተክዬ*--ሰው መሃል፤ *ትኩ*--ደስ የሚል ነገር ሰርቶ ሲያስደነግጠኝ፣ *ትኩነት*--የምፈልገውን አንዲያደግልኝ (ለምሳሌ ውሃ እንዲያቀብለኝ)፣ *ትኪ*--እንደላይኛው ምሳሌ ይሆንና ግን ሲደግመው፣ *ትት*--እስከ አምስት ጊዜ ተደጋግሞ ወይም የበለጠ፤ የወሲብ መደምደሚያ ላይ፣ *ተት*-- እንደላይኛው ግን ቀለል ሲል፤ *ትዬ*--ለሁለት ሶስት ወይም ለበለጡ ቀኖች ፊልድ ስራ ሄዶ ሲመለስ፣ ዘልዬ አንገቱን አቅፌ አይኖቼን ጨፍኜ የምለው፣ *ትክ*--ትንሽ ሲሳሳትና ስቆጣው፣ *ተኪ*: ሳባብለው (ያልተደረበ *ትኪ*)::

ሲሰማ ብሄር ብሄረሰብ፣ ዲሞክራሲ፣ እኩልነት ምናምን ትግል ምናምን: *ባክሽ ይሄን ነገር ዝጊና ከድብርት ገላግይኝ* ይላል:: ጎኔ ተቀምጦ ወይም ጋደም ብሎ ሲነካካኝ ሲደባብሰኝ እወዳለሁ: የሴትነቴን ጨዛና ልስላሴ በዳበሳ ካልፈተሸ፣ የፀጉሬን እርዝመትና ጠረን በበከንፈሮቹና በአፍንጫው ካላጠና፣ የቅንድቤን ፀጉሮች በቀስታ ቆጥሮ ካልጨረሰ ምናምን:: እንዲያ እንዲያ ካላደረገኝ ጎደለ ማለት ነው::

ግን ተለወጠ::

ወሲብ ሲያደርግ ልክ የተቀጠረበት ስራው መሰለ:: እልህና ቁጣ አለበት:: ከእኔ መራቁን ሊደብቀው ቢሞክርም፣ ድርጊቱ ውስጥ ተሰግስጎ ብቅ ጥልቅ ሲል አያለሁ:: ወሲብ እልህ አለው? ቁጣው ለምንድነው? *ተክዬ የግንባርህ ቆዳ ለምን ይሰበሰባል?* ይሄ ችሎታ ተብሎ ሳላገባው በፊት ታላላቆቼ ሲያደንቁለት ሰምቼአለሁ:: በራሴ ስሜት ተንከረባብቼ እሱ እንዲደርስብኝ ስጠብቅ ሁለመናዬ ይዝላል: እንዲተወኝ እፈልጋለሁ:: ግን ገፁ ላይ የማየው ያልለመድኩት ጎምዛዛ መልዕክት እንዳይመጣ አፌን አቀብኩ:: ይሄ አዲስ ጉዳይ ነው:: ከተኛኝ በሁዋላ አለመተኛት ጀመርኩ:: እንቅልፍ የማጣበት ሰአት ተደጋገመ:: ምክንያቱም ተኮሳ በምንም ምክንያት እንዲርቀኝ አልፈልግም:: የማስበውንና በመንፈስም በስጋም የሚያስጨንቀኝን በግልፅ ለእሱ አለመንገሬ ተኮሳን የፈራሁት አስመሰለብኝ፣ ቢያንስ ለራሴ:: ይሄም አዲስ ጉዳይ ነው:: የሆነ የተበላሸ ነገር አለ:: *'አታስጨንቀኝ፣ ምን የሆንከው ነገር አለ?'* አልኩት:: ደጋግሞ ስላሳሰበኝ ደጋግሜ *'የሆንከው ነገር አለ ንገረኝ'* ስለው:

*'ምንም'* ይለኛል::

የማደርገው ቅጡ ጠፋኝ (እማማ እንዲህ ትል ነበር) ትምህርቴን ጨርሼ ዲፕሎማዬን ሳልይዝ ልጅ እንውለድ ተባብለን ኪኒን እውጣለሁ:: በቃ ቢዞርብኝ:

---ልጅ እንውለድ ተክዬ አልኩት

እንዲህ ስለው፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ፊቱ ላይ ወደ ንዴት የቀረበ ነገር አየሁ:: ከዛ:

---አሁን ለምን ፈለግሽ? ትምህርቴን ልጨርስ ስትይ አልነበረም?

---አብረን የወሰነው ነው አዎ:: ቅር ካለህና ሃሳብህን ከለወጥክ ማለቴ ነው

---ያልሽው ካልተደረገ እኮ ያዙኝ ልቀቁኝ ትያለሽ *አልልም:: ብዬ አላውቅም:: ውሸት ነው::*

የገፁ ሁኔታና ይሄ አባባሉ ተደምረው ምን አንደሆነና እንደተፈጠረ ባላውቅም ትልቅ ችግር ውስጥ እንዳለሁ ተረዳሁ:: እንጀቴ ነደደ:: አንዳንዴ እስኪነጋ እንቅልፍ አይጠጋኝም:: ልቤ *ዞረሽ እቀፊው ዞረሽ ሳሚው* ይለኛል:: ግን ፈራሁት::

ራሴን እንዲህ አቁሜው (እሱ አፍ እንዳልደርስ፣ እሱ ዕንቅልፍ እንዳልገባ) አላውቅም:: ስንቴ ነው ከጥልቅ እንቅልፍ የቀሰቀስኩት፣ *ሶትተኛ ሶኔ ሶልተኛሁም* እያልኩ እየተላፋሁት:: እንቅልፍ እንኩዋን ቢወስደው እየነካካሁ ቀስቅሼ በጠራራ ሌሊት የሆነውን:: ቢዘጋኝም ልጠራው ይከጅለኛል ……ማጅራቴ ላይ ትንፋሹን እየሰማሁ ነፍሴ እንዴት እረፍት ታግኝ?

የሚያስቀይም ነገር እንዳላደረኩት አውቃለሁ:: አሁን የፈራሁት ወሬኞችን ነው:: ተኮላ በሰፈር የመረጃ አሰባሰብ ስልት ስላደገ፣ ማለቴ እያወራና እየተጫወተ በፈጠራ አሉባልታ ሊጠመጠም እንደሚችል እገምታለሁ:: በቀላል አማርኛ ወሬኛ ነው:: ግን ፍቅር ከዚህ አይከልለኝም? ፍቅር ወሬን የሚከላከል ጋሻ የላትም? ልክ እንደ ኤሊ ከወንጭፍ የሚጋርድ ጥሩር አለበሰችም?

*　　　*

ተኮላ የሴት ጉዋደኛ እንዲኖረኝ አይፈልግም:: በትክክል ምንም አይነት ጓደኛ እንዲኖረኝ አይፈልግም:: ምክንያቱም ሴቶች በእሱ ልምድ በቀላሉ በጓደኛቸው ተጠዝጥዘው ማውጣት የማይገባቸውን ወንድ ሲያወጡ ስላየ ነው:: የቀመሱትን ቆሻሻ ወንድ ቀምሰው ልክ እንደ እነሱ ጉዋደኛቸው እንድትቆሽሽ የሚያሴሩ ወይዛዝርት እንዳሉ ያውቃል:: አንዱ የፈለጋትን፣ ግን እምብዛም ያልፈለገችውን ሴት ወይም አይታው የማታውቀውን ሴት ሊያወጣ ሲመኝ፣ በሚያውቃት ሌላ ሴት በኩል ፕሮፓጋንዳ ተነፍቶለት እንደምትወጣ ያውቃል:: ማለት አንዲትም ጉዋደኛ ብትሆን ለተኮላ እኔ ላይ አደጋ የማድረስ አቅም አላት:: እንዲህ እንደሚያስብ ባውቅም እንዳላወቀ እየሆንኩ፣ በትንሹም ቢሆን በመቅናቱ ደስ እያለኝ ኖሬአለሁ:: *የሚቀና ሲያሳጣዎት* ብዬ ሳልተርት አልቀርም::

*ታዲያ* ግን ትምህርትቤት እያለሁ ከብዙ ሰው ጋር እየተማርኩ ቢያንስ አንድ ሁለት ጓደኞች ቢኖሩኝ ለብዙ ነገር ይጠቅሙኛል:: አሞኝ ከትምህርት ቤት ብቀር፣ አለ አይደለ፣ ምን እንዳመለጠኝ የሚነግረኝ ተማሪ መኖር አለበት:: በዚህ ምክንያት ለተኮላ

ሳልነግረው አንዲት ምትክ የምትባል ወዳጅ አፍርቼአለሁ:: ጓደኛዬ ብቻ ሳትሆን ስነስርአት ያላት ጎበዝ ተማሪ ስለሆነች በአንዳንድ ነገርም ትረዳኛለች:: ከምትክ ጋር ብዙ የተለያዩ ጉዳዮች ብናወራም፣ ስለተኮላ አዲስ ፀባይ ልነግራት ፈራሁ:: በመጀመሪያ በእኔና በእሱ መሃል የሆነ የተበላሸ ነገር እንዳለ ባምንም፣ ምን እንደ ተበላሸ አፍ አውጥቶ ስላልነገረኝ የሚወራ አልሆነም:: እና ተደበርኩ:: የእውነት ግን ለምትክ ባለመንገሬ እንኩዋን ቅር አላለኝም:: ምክንያቱም ምትክን ብዙ ነገር እደብቃታለሁ:: እሷም ቀላል ነገር ካልሆነ እንደምትደብቀኝ አውቃለሁ::

በአለም ላይ ያሉ ቆነጃጅት ጥቂት ናቸው:: ሁሉ ቆንጆ አይደለም:: ሁሉም ሴቶች ሁሉም ወንዶች ቆንጆ ይፈልጋሉ:: ለመመደብ እንዲመቻቸውም አለ አይደለ አንዳንድ መመዘኛ ዝርዝር አውጥተዋል:: እኔ ብዙውን የሚሟላ ብሆንም ተኮላ እንደወደደኝ ካወቅሁ በሁዋላ ግን ግድ አይሰጠኝም ነበር:: ይሄን አይነት ወሬ በመድገሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ:: ወደ ምትክ ልመጣ ነው:: ምትክ ቆንጆ አይደለችም:: ማንም ሲያያት ቆንጆ እንዳልሆነች ያኔውኑ ያውቃል:: ክርክር የለም:: ጎደላት ብዬም ልታዘባት አልችልም:: በእግዜር ስራ? ምን አግብቶኝ በእሱ ሰራ? ምን ቆርጦኝ::

ግን ጎራዳ መሆንዋን እንዲህ አደባባይ እያየው አይኑዋን በጨው አጥባ ልትክድ ትፈልጋለች:: በጨዋታ መሃል በራስ የመተማመን ጥበቧ ልክ እንደ ቆንጆ እኔን ከእሷ አስተካክላ ስታወራ ፊቷ ላይ ሃባ ቅሬታ የለም:: ምንም አልላትም:: ምትክ በትምህርቷ በጣም ብሩህ ልጅ ሆና ለምን እንዲህ እንደምታስብ ለዘላለም አይገባኝም:: አንዳንዴ ‘ጤንነት ይበልጣል’ እያልኩ በሽሙጥ መስመር ከሳተ አመለካከቷ ልመልሳት ብለፋም፣ ወይ አልገባትም ወይ አውቃ ተኝታለች:: ቀን ቀን የቤት ሰራተኝነት እየሰራች ማታ ማታ የምትማር ደሃ ልጅ ናት:: ‘መማርና መሻሻል እሱ ነው ዋናው’ እላታለሁ:: ጆሮ ግን የላትም:: እንዴት ሰው አንጎል እያለው ጆሮ የለውም? ወይም ጆሮ እያለው አንጎል የለውም:: ሁለቱም ያለው ማርያምን አላጋጠመኝም::

ማስረጃ እንደሚጠሉ ባውቅም ማስረጃ ላቅርብ: አንድ ቀን ማታ የመጨረሻ ክላስ አስተማሪያችን ቀርታ ከትምህርት ቤት ወጥተን ከግቢ ውጭ ቆመን ስናወራ አንድ ሰፈሯ የሚያውቃት ልጅ (ስሙ ትዝ የማይለኝ ገምጭ ቢጤ) እየጮኸ ስሟን እየጠራ ወደ ነበርንበት

መጣ:: እኛ ጋ ከደረሰ በሁዋላ 'ታዲያስ ከቤ ደህና ነሽ' እያለ ሊያቅፋት እላይዋ ላይ ወደቀ:: በማፈር፣ በመደበርና በመብሸቅ ቸል ያለ ሰላምታ ስትሰጠው አየሁ:: ደግነቱ ብዙ ሰው አልነበረም:: ማለት *ከቤ* የሰፈሯ ስም እንደሆነ አልነገረችኝም:: ምክንያቱም ሴት ሆና ወንዳወንድ መምሰል እንደገና ወንዳወንድ በመሆኗ 'ከቤ' መባል የምትወድ ሴት የለችም:: በቀላሉ *አንቺ አስቀያሚ* ማለት ነው:: እኔን ቢሉኝ (አይሉኝም እንጂ) አቀምሳለሁ.......

*ያን ዕለት መሽቶ ነበር::* ልጁ ሰላምታ ብሎአት (ወይስ ሰድቧት ልበል) ከሄደ በሁዋላ ማልቀስ ጀመረች:: ቢዘገይም ላፅናናት ቡና ልጋብዝሽ አልኳት:: ሰፈሯ የምታደርሳት አንዲት ዙፋን የምትባል አሰሪዋ እወዲያ የመኪናዋን ሞተሯን አስነስታ እየጠበቀቻት ነው:: የከቤ ለቅሶዋ ስለበረታ እንደ ልጅ አቅፌ እያባበልኩ መኪናው ውስጥ አብረን ገባን:: ሶስት ሆነን የሆነ ካፌ አርፈን ወፋፍራም ቡና አዘዝን:: አያስቸኩለኝምና ልክ ከትምህርትቤት በምንወጣበት ሰአት ሊፍት ሰጥተውኝ፣ ተኮላ እቤት ገብቶ እንደሆነ እንዳያየኝ *ቤቴ ያለበት ቦታ መኪና አያስገባም* የሚል ሰበብ ፈጥሬ ሁልጊዜ አውቶቡስ ወይም ታክሲ የሚያወርደኝ ቦታ ጣሉኝ::

ምትክ *ከቤ* መባሏ የሚገርም አይደለም፣:: አንደኛ ሁልጊዜ የምትለብሰው ለቀቅ ያለ ሱሪ ነው:: ተኮላ ስለ ሴት ያውቃል እና *ሱሪ የምትለብስ ሴት ሴት አትመስለኝም* ይላል:: ሁለተኛ ሁልጊዜ *ስራ ይቀንስልኛል* ስለምትል ፀጉሯን ትላጨዋለች:: ገሬድና ረዥም ፀጉር አይስማሙም:: *ታዲያ* ትንሽ ከዳሌዋ ለአመል ሰፋ ባትል ወንድ ነው የምትመስለው:: እሷን አቅፌ ሁለመናዋን የሸፈነውን የጢስ፣ የጋዝና የበርበሬ ጠረን እየማግሁ ሳባብላት የተሰማኝ ምንም ከሌሎች ጋ ወዳጅ ብንሆንም ደብቀን የምናስቀምጣት ሚስጢር ነገር እንዳለች ነው:: የምንፈራት፣ የማናወራት፣ ገበና እንዳለችብን ነው:: *ከቤ* ለራሴ ጥርሰ መልካም፣ አካሄደ ንቁ፣ ረዥም ጥቁር ጠይም ናት:: ይሄ አይታያትም:: የሚታያት ሌላ ሴት የሚፈልገውን መምሰል ነው:: በቁንጅና ያልተገኘ በቀልጣፋነት እንደሚረታም ይሳታታል::

አዎ:: ከሰዎች ጋር ስታወራ ነገር ቶሎ ይገባታል:: ክፍልም ውስጥ ማርኳ ከብዙዎች ይሻላል:: ግን ስለ ሴትነቷ አታውቅም:: አንዴ እንደውም (ተደነቀ ሲለኝ) ከወንድ ጋር ምንም ግኑኝነት ሳታደርግ *አረገዝኩ* አለችኝ:: የማይታመን ነው አይደለ? የአስር አመት ልጃገረድ እንደሆነች ሁሉ ማርገዝ ዝም ብሎ

በባዶ ሜዳ ያለ ወንድ ግኑኝነት እንደማይመጣ እኛ ሰዎች እንጂ ዶሮዎች እንዳይደለን ዘርዝሬ አስረዳሁዋት:: በመጀመሪያ ወንድ አይቀርባትም:: አለ አይደለ በቃ ምኞቷን ወይም ቅዠቷን ያወራች መሰለኝ:: እንደውም የመረመራት ዶክተር ችግሯ የሆነ የእንግሊዘኛ ስም እንዳለው ነገራት:: ነግራኝ ረሳሁት:: አምስት ወር ቆይቶ እርግዝና የሚባል ነገር ሆዷ ላይ አይታይም:: ታሕሣሥ መሃል ላይ ነግራኝ ሚያዚያ ውስጥ ሆዷ ለአመል እንኳዋን አላበጠም:: ከምታሰራት ያቺ ዙፋን ካልኩዎት ሴት ጋር ሄደው ቼክ ምናምን አደረጉ:: 'እና ተሳስተሻል አይደል' አልኩዋት:: 'አዎ ላብራቶሪ አበላሽቶ ነው' ምናምን አለችኝ:: 'ያን ነገር እውነት አድርገሽ አታውቂም?' ምናምን ስላት፣ 'ከሚወደኝና ከምወደው ጋር ካልሆነ ለምን ብዬ' ምናምን ብላ ጉራ ቢጤ አለ አይደለ ቸረቸረችልኝ:: እንዲሁ ኖራ፣ በአርባ አመቷ ሞተሯ ከወረደ እገረማለሁ:: ግን አላልኩዋትም::

በሚያብረቀርቀው ጌጣ ጌጥ ስር፣ የማናየው ተራ ነገር አለ:: ወይም ተራ የመሰለ:: ዋናው አለም ከሚያየው እምነታችንና ፍላጎታችን ስር፣ ይሄን ዋና እምነትና ፍላጎት ዘርሮ የሚወጣ ድክመት ያንቀላፋል:: እዛም እንዳለ እናውቃለን፣ እዛም እንዳለ አናውቅም:: ምትክ ብሩህነት ስር፣ ምትክ ሃይለኛነት ስር ለቅሶ እንዳደፈጠ የገባት እኔ ብቻ ነኝ:: በእኔና በተኮላ የፍቅር ምንጣፍ ስር፣ በካቡል ምንጣፋችን ከተዋበው ወለል ስር ምን ተባይ ይነቃነቃል? ምን ተንቀሳቃሽ ይላወሳል?

በትክክል ተኮላ መቼ ይቀየመኝ እንደጀመረ አለማወቄ ሳይጎዳኝ አልቀረም:: ይሄ ሽሽቱ የጠቆመኝ ነገር ቢኖር ተኮላን እንደምፈራው ነው:: የተለወጠበትን ምክንያት ዘርዝሬ ልጠይቀው አልጣርኩም:: ለምቦጩን ጥሎ ሲመጣ ለምቦጩን ለመሰብሰቢያ እንደማንም ሴት በወሲብ፣ በተራ ጥያቄና በ *ኦይዞህ* ላባብለው መሞከሬ ራሴኑ አሳዘነኝ:: ለሁሉ ግን ጊዜ አለው:: ለሰቀቀንና ለመሳሰሉትም::

* *

ተክዬ ናዝሬት ስራ አለብኝ ብሎ ከሄደ ሁለት ቀኑ ነው:: ቅዳሜና እሁድ ከሄደ ሰኞ ወይም ማክሰኞ ተመልሶ ይመጣል (ከቀናው):: እሱ ጠዋት ሲሄድ እኔ ተከትዬው ተነስቼ እንደ ድሮዬ አትክልት ቦታ አልወጣሁም:: እውጭ በረንዳ ላይ ቋንጤ ወንበር ላይ ተቀምጬ ተደብሬ ቁርሴን አየበላሁ፣ አላማ ቢስ እንደ ሆንኩ ሁሉ ምንም የማያሳየኝን የልቤን ደብተር

ሳነብ አረፈድኩ፡፡ ብዙ ጊዜ ጠዋት ጠዋት የማዳምጠው ሙዚቃ አላሰኘኝም፡፡ ቤቱ ብቻ ሳይሆን ግቢው የእኔ አልመሰለኝም፡፡ ከቤት ልወጣ ዞር ብዬ ሳይ (በስተግራዬ ነው አትክልቱ) በነዛ ተክሎች መሃል መሃል በተዘረጉት ሁለት እግሮች ብቻ በሚያስቆሙት ቀጫጫ የሳር መንገዶች ውስጥ አልፌ አንዳልነበረ ሁሉ ተሰማኝ፡፡ ያቺ የመሬት ቁራጭ በመስኮት ክፈፍ የተቀፈፈችው ከሌላ አገር የተላከች ፎቶ ናት ቢሉኝ አይሰቀጥጠኝም፡፡ (ራሳችንን እንድንጠላ የሚደረገው በዚህ ስልት ይሆን?) የሆነ አስፈራሪ የስሜት ዝባጭ ውስጥ ነበርኩ፡፡

በዛን ሰሞን ደሞ ምትክ ሆና የማታውቀውን የዙፋን ባለቤት ስለታመመ ተደበርኩ እያለች የበለጠ ትደብረኛለች፡፡ አንድ ቀን አከታትላ በመቅረቷ ወይም ብቻዬን መሆኔ ተሰምቶኝ ሳይሆን አይቀርም በጎረቤቷ የሱቅ ስልክ ደወልኩላት፡፡ ከዛ በፊት ደውዬላት አላውቅም፡፡ ከዛ በፊት ለዘላለም አጠገቤ ይኖራል ያልኩት ተኮላ ብቻ ነው በሃሳቤ የነበረው፡፡ እና ለምትክ ደውዬላት፣ አምስት ደቂቃ ያህል ጠብቄ ስትቀርብልኝ፡

---እኔ ምንም አልሆንኩም፤ ግን እኛ ታመዋል ያልኩሽ ሰውዬ ዛሬ ጠዋት ሞቱ፡፡ አልመጣም አለችኝ፡፡

ላስተዛዝናት የቤቷን አድራሻ ፍጥጥ ብዬ ጠየቅሁዋት፡፡ ቀብሩ ዮሴፍ አስር ሰአት ላይ እንደሆነ እዛው ቀብሩ ላይ ልታገኘኝ እንደምትችል ነገረችኝ፡፡ እንዲህ ስትደባብቅ መሄድ አልፈለኩም ነበር (ባታስብም መሰለኝ)፡፡ የምትንገበገብለት አንድ ሰው ሲሞት ቀብር አለመድረስ ስነ ስርአት አልመሰለኝም፡፡ በለቅሶ አመሃኝቼ የምትደብቀኝን ነገር ማየት ደሞ ጓጓሁ፡፡

---ተክዬ ደሞ ስለሌለ ቤት ምንም አልሰራም እመጣለሁ አልኩዋት

---ጥሩ እንደውም ቤቴን እግረመንገድሽን ታያለሽ አለችኝ

---ጥሩ ግን መልሼ የእኔን ላላሳይሽ እችላለሁ፣ ምክንያቱም ተኬ *‘ሰው አታምጭብኝ’* ይላል ታውቂያለሽ አይደል? አልኩዋት

---ይገባኛል፡፡ ምንም አይደለም፡፡

ግን ያን ቀን የማላውቀውን ሰው በደንብ ከማላውቃት ጋር እያለቀስኩ (ማልቀሴ አይቀርም ስታለቅስ

t.me/BooksandYou

ካየሁዋት) ልቀብር ሄጄ ማየት የማልፈልገው ነገር ስላጋጠመኝ ቆጨኝ:: እንዲህ ነው ሲስፋፋ:
የቀብሩ ዕለት ከባቡር ጣቢያ ስታድዮም በውይይት ታክሲ ወደ ንፋስ ስልክ ጉዞ ጀመርኩ:: መሃል መንገድ ላይ የምንዝበት ታክሲ አንዱ የሁዋላው ጎማ ፈነዳና ወይም ተነፈሰና እሱ እስኪቀየር ወይም ተሰባሪውን ታክሲ ተክቶ የሚጭነን ሌላ ታክሲ አስኪመጣ ተሳፋሪዎቹን ዳር ይዛችሁ ጠብቁ አሉን:: ከመጠበቅ ይልቅ በእግር ትንሽ ልነቃነቅ ብዬ ሳዘግም፣ አንድ አስር ደቂቃ አለፈ:: ሌላ ታክሲ ጣቢያ ደረስኩና ሌላ ውይይት ይዤ ወደ ዮሴፍ መንገድ ጀምሬ ዘ ድሬክ ሆቴል (ከተኬ ጋር እዚህ አንድ ሶስቴ መጥተናል) አጠገብ ታክሲው ሰው ሊያወርድና ሊያሳፍር ሲቆም ያልጠበቅሁትን ነገር አየሁ::
ከሁዋላ ተቀምጫለሁ:: ተሳፋሪው ሁሉ የተከዘ ይመስላል:: የተዝናናሁ ስለሆንኩ ያለሁበትን አካባቢ ዞር ዞር እያልኩ በጉጉት አያለሁ:: ከፊት ለፊቴ በወዲያኛው መስታወት ውስጥ ከሩቅ ሁለት የውሃ ላስቲክ ጠርሙሶች የያዘ ሰው ሲሮጥ አየሁ:: ልቤ ደነገጠ:: ምክንያቱም ተኮላ ሲሮጥ አይቼው አላውቅም:: ልብ ስልና ስፈልግ ከታክሲው ፊት ለፊት ነጭ የመስሪያ ቤት መኪናው ቆማለች::
*ናዝሬት አይደለም ያለው:: ተመልሷል?*
ይሄ ብቻ አይደለም ያስደነገጠኝ:: ማለት ከናዝሬት መመለሱ አለመመለሱ:: ስራውን ጨርሶ ከአንድ ሰአት በፊት አዲስአባ ገብቶ ሊሆን ይችላል:: ያስደነገጠኝ አንዱን የላስቲክ ውሃ ወስዶ ጥቁር ለብሳ ብቻዋን ተቀምጣ ለነበረች ሴት ሲሰጣት ነው:: ከዛ ጎንዋ ፈገግ ፈገግ እያለ ተቀመጠ:: ውስጤ ተንቀጠቀጠ:: ሆዴ አስገመገመ:: ራሴ ስህተተኛ እንደ ሆንኩ ሁሉ አይኖቼን ከተኮላና ከሴትዮዋ ቶሎ መለስኩ:: ምራቄ ትን አለኝ::
ታክሲው ተነስቶ መንገዱን ሲጀምር ጎሮሮዬ አስኪሰነጠቅ እየሳልኩ አይኖቼን ተኮላ ወደ ተቀመጠበት ወረወርኩ:: ሴትዮዋ ጎን ሆኖ በሌላ በሌላ ነገር ከሚፈልጋት ሴት ጋር እንደሚያወራ አይነት ወግ ይዟል:: ይገባኛል የዛ አይነት አቀማመጥና የአወራር ቅጥ::
ወደ ሁዋላ ወያላውን ዞር በልልኝ ብዬ ሳይ ተኮላ ከሴትዮዋ ጋር ተቀምጦ ይስቃል:: ጥርሶቹ ባይታዩኝም ይስቃል:: በእኔና በእሱ መሃል ኳስ የያዘ ልጅና ተሳፋሪዎች እየከለሉኝ ብዙ አስመራሪ ነገር

ለማየት ስንጠራራና ስወጣጠር አጠገቤ ያሉ አንድ አዛውንት አጉዋጉል ገፋሁ:: ገላመጡኝ:: ከመገልመጥ አልፌአለሁ:: መገልመጥ ምንም አይደለም አሁን:: ዝም ብዬ ታክሲውን 'አቁምልኝ!' አልኩና ያጋጠመኝ ቦታ ወረድኩ:: ወደ የት እንደምሄድ አላውቅም:: የብዙ ለቀስተኛ ሰልፍ ተኮላና ሴትዮዋን ከለለኝ:: ተኮላን አስቀይሜው አላውቅም:: በልቤም አላመነዘርኩም:: ተኮላን ከብዙ ሰዎች የበለጠ እወደዋለሁ:: መጀመሪያ ወደ የትም መሄድ አልፈለኩም:: በድንገት ወሃ ጠማኝ:: ውሃ መጠጣት ግን አልፈለኩም:: ወደ ሁዋላ ዞር ስል አንድ ካፌ አየሁ:: በሩ ላይ በትላልቅ አረንጉዋዴ የኒዮን ፅሑፍ *እንቁጣጣሽ ኬክ* ቤት ይላል:: ወደዛ በፍጥነት ሄድኩና ሰው የሌለበት ጥግ ተቀመጥኩ:: ለብቻዬ ማውራት ጀምሬአለሁ:: ራሴን ለመቆጣጠር ስለፋ አንዲት ልጅ-እግር ሴት መጥታ ፊት ለፊቴ ቆመችና:

---ምን ልታዘዝ? አለችኝ

---ለስላሳ

---ምን?

---ኮካ

---ከፍሪጅ ውስጥ ወይስ……

---ደስ ያለሽን::

አፌ ላይ ልትወጣ የምትታገለውን *አትነዝንዥኝ* የምትለዋን ቃል ዋጥኩ::

* *

ተኮላ በሁለተኛው ቀን ማታ ሰኞ ዕለት ቤት መጣ::

---ከናዝሬት አሁን ገባሁ:: መንገዱ ገሎኛል:: አራት ቀን ናዝሬት ፀሐዩ እኮ ይገልሻል:: የሚበላ ቶሎ አምጭልኝ አለኝ::

ምንም እንደማያውቅ ዝም አልኩት:: ዞር ብዬ ግን ማድቤት፣ መፀዳጃ ቤት ብቻዬን በሆንኩበት ቦታ ሁሉ አለቀስኩ:: ደጋግሜ አለቅሳለሁ:: 'ናፍቀሽኛል' ብሎ ወደ አልጋ ጎትቶ ሲወስደኝ የውሸቴን 'እኔም' እያልኩ ተጎተትኩለት:: እንደውም አልጋውን አመቻቸሁ:: በምሰራውም አፈርኩ:: ለምን አልፈር? 'ይቅርብሽ የማይሆን የማይሆን የለመደ ነው' ያለችኝ ባህሬን የሄደችው ሃና ትዝ አለችኝ:: እግዚአብሄርዬ ይሄን ያየሁትን፣ በመኖር ላይ ያለሁትን ውሸት እንዲያደርግልኝ ተመኘሁ:: ውስጤን የሚያይ የለም እንጂ፣ በየዋህነት፣ በእውነትና በትህትና ወድጄዋለሁ:: ትህትና፣ እውነት፣ የዋህነትና ቅንነት አካል ቢሆኑ ቢገዙ እንዴት ያምር ነበር? የዋህነትና እውነተኛነት ሲከስሩ 'ቂልነት' ይሉአቸዋል:: ግን

አይደለም:: ቂል አይደለሁም:: ብወደውም ግልፅ ልሁንና የእንጀራዬ ነገር ከበደኝ:: ተኮላ ሁሉ በእጁ፣ ሁሉ በደጁ ነውና ተበሳጭቶ ቢያባርረኝ ትምህርቴን እንደማቆም፣ ታግዬ ብጨርስ እንኳዋን ስራ የሚያስቀጥረኝ የማውቀው ሰውና ዘመድ እንደሌለኝ አውቃለሁ:: ያን ቀን ማታ ቂጤን እንደ ሸርሙጣ ቸብ እያደረገ *ምነው አንድ ቀን እንኳዋን ብታጎነብሺልኝ* አለኝ......ተቃቅፈን ተሳስመን እንደሆነው እንሆናለን እንጂ አፉን ከፍቶ እንዲህ ብሎኝ አያውቅም:: የፍቅር አቅጣጫ ስም የለውም::

የትራሴ የጨርቅ ሰንበር ጉንጬን ይፍቀኛል:: በግራ አይኔ የመስኮቱ የጥበብ መጋረጃ ጥለት ላይ ያረፈች ጥቁር ቢራቢሮ አያለሁ:: *ምን ልታደርግ መጣች?......የአትክልት ቦታውና አበባው እዛ ሆኖ መኝታ ቤት ለምን ትገባለች?......የጥለቱ አረንጉዋዴ ቅጠላ ቅጠል መስሎአት ይሆናል......ተኮላ ባይጫነኝ ተንጠራርቼ ቢራቢሮዋን መንካት ፈለኩ......ቀስ ብዬ አንስቼ በመስኮት እንዳትጎዳ አደርጌ በመስኮት ስወረውራት......በሕመም አይሮፕላን እየሄድኩ ነው......በበሽታ ሄሊኮፕተር ......ቢራቢሮዋ ወደ ላይ የምትንሸራተት ትመስላለች......ወደ ላይ እንዴት መንሸራተት ይቻላል?......አለችበት አንዴ ዞራ ወደ ታች ተዘቀዘቀች......ትን አይላትም?......ግራና ቀኝ የተዘረጉት ክንፎቿን በትንሹ ላይና ታች በቀስታ አራገበች......የምትበር መስሎኝ ነበር......'እፍ' ብዬባት እንድትነሳ አንገቴን ከተንበለበልኩበት ወደ ዛ እንደ ቀጭኔ መጎተት ብችል......የት ትሄዳለች? ረዥም ማታዎቿን እንዲህ አበቦች ስር በፀጥታ ተለጥፋ ስታሳልፍ አሰብኳት......አበባና ቅጠል ለመሬት እግዜር የሰጣት የጥበብ ልብስ አደሉ?......ከአበባ የበለጠ ምን ይታመናል? ይነካል፣ ይታያል፣ ይሸተታል፣ ይበላል፣ ይጠጣል......መስታወትና ሲሚንቶ ከሞላበት ከተማ ላይ አንዴት ለስላሳ ሆነው በቀሉ?*

---እንዴት አወቅሽበት? አለኝ:: አፌ ምንም አላለም:: *አልገባህም:: መንበርከክ ቁም ነገር ነው?*

ተኮላ በስሜት ይገፋል......ቁና ቁና ይተነፍሳል:: ጠረኑ ጀርባዬ ላይ እንደ ዝናብ ይወርዳል......ፊኛዬን ግራና ቀኝ ያመኛል:: አይኖቼ በእንባ ሞልተው(አሁንም ይሄን እያወራሁ ሞልተው) እርም አላቅምና፣ እንዳይሰማኝ አድርጌ፣ በተንጋደደው ሁለመናዬ በልቤም እዘፍንለታለሁ......*እኔስ አንተን አንተን የልጅነቴን......ፍቅር እንደ ሀሁ ያስተማርከኝን......* ምክንያቱም ስለምወደውና

ስለሚያበሽቀኝ……እኔስ አንተን አንተን……..አፍቃሪ ነኝ ብዬ ባስብም፣ ለዘመኑ አልነበርኩም፡፡ (የእሱን ስሜት እንጃ እንጂ) የሞቀ ስጋ ሳይሆን ጎምዛዛ አየር ነበር ሁለመናዬን የሞላው፡፡ ተኮላ አንዳንዴ የማያምር አባባል አለው፡፡ የሆነ የጎዳና የመሰለ አማርኛ፣ የዱርዬ ምናምን፡፡ ያልተመቸችው ሴትዮ ካጋጠመችው ‘ይህቺ ቁንጢቢራ’ ይላል፡፡ ቃሉ ባይወጣውም እንደዛ ከሚሰድባቸው እንስቶች አንዷ የሆንኩ መሰለኝ፡፡

ሰሙኝ?! ሰሙኝ? *ሚርትዎ ሰመረልዎት? ድሮስ የት ሊደርስ?* ብለው ፊትዎን ዞር አድርገው ጌኛዊ አልሳቁም?

ሰው ሁሉ በሽታው ራስ ወገቡን ነው.......

ተኮላ መንገድ ዳር ቶዮታ ክሩይዘሩን አቁሟል:: ተመሳሳይ ጥቁር ቀለም ያላቸው ሱፍ ኮትና ሱሪ ለብሷል:: በቀጫጭን ብርቱካንማ ሰንበሮች የተዝጎረጎረ ክራቫት አስሯል:: ሸሚዙ ቀይ ነው:: ቀኑ ሞቃት ስለሆነ ይሁን ወይም ለመዘነጥ የክራቫቱ እስራት የላላ ነው:: አልፎ አልፎ ድምፅ ሳያሰማ በትንፋሹ ብቻ ያፏዋጫል:: ሁሁሁእ ሁሁሁእ:: ይሄ ልማዱ ዕድሜው ገና ሃያ ሳይገባ የነበረ ነው:: መሳሳት የጀመረ ሉጫ ፀጉሩን የተቆረጠው በአጭሩ ነው:: እንዲህ በመቆረጡ አተኩሮ ላላየው እድሜው እንኳን ሃምሳ አርባ የገባ አይመስልም:: ከአፍንጫው ስር በቅባት ይሁን በላቡ የሚያበራ ዞማ ጢም አለው:: ግራ እጁን ሱሪ ኪሱ ከቶ መኪናውን በቀኝ እጁ ክርን ተደግፎ ቆሟል:: አልፎ አልፎ ከመኪናው ንጣት ላይ ቆሻሻ እንደሚያነሳ ሁሉ በኮቱ አጀታ ነጩን ብረት ይወለውላል:: ከአፉ ባይወጣውም በድርጊቱ ልክ የራሱ እንደሆነ ሁሉ የመንግስት መኪና በመንዳቱ ይኮራል:: የመኪናው ንጣት ከለበሰው ጥቁር ሱፍና ከረዥም ሸንቃጣ ቁመናው ጋር አድመው ባለስልጣን ያስመስሉታል:: ሾፌር ነው ብሎ የሚጠረጥር የለም:: በተቀጠረ በሁለተኛ

ሳምንቱ ይሄን ፀሐይ ውስጥ አንደ መስታወት የሚፈልቅ፣ ንጣቱ ወተት የመሰለ መኪና እየነዳ አንጀባ አድርጓል፡፡ ከአንድ አመት ተኩል በፊት ያገባት ሚስቱን፣ ሙሽርነቷ ገና ሳይበርድ፣ ጎኑ አስቀምጦ፣ ከጎጆ ቤት አስከ ወሎ ሰፈር፣ ከዛ ከሳሪስ በቦሌ ወደ መገናኛና ገርጂ፣ በመካኒሳና በላፍቶ አንድ ሁለቴ አመላልሶ 'ባልሽ ቀላል አይምሰልሽ' አይነት ፎልሎ ነበር፡፡ ክርኑን ለዝነጣ በመስኮት አውጥቶ ያልተረበው የውይይት ታክሲ ሾፌር(*እብዶች!*)፣ ያልረገመው ወያላ (*አቃጣሪዎች!*)፣ ያልተቸው መኪና (*ትዊስት ሲደ፣ነስ የገዛሃት ናት?*)፣ ያላጣጣለው ሰላማዊ ሾፌር(*እንቅልፋም!*) አልነበረም፡፡ እዚህ መኪና ውስጥ ተቀምጦ እዚያ ከሚያየው ሻገር ሆቴል በሞቀ አየር ውስጥ እየተመመ የሚመጣው የመፅሃፊ ዶሮ፣ የህብስትና የቡና ጠረን፣ የሰርጉንና የጫጉላ ማታውን ያስታውሱታል፡፡ እሱ 'ለጋራ ደስታችን' ብሎ ሲሰክር ሙሽሪቱ ጅማ ወርቅ (ምላሱ ቅቤ ውስጥ እንደተነከረች ሁሉ ለስልሳ በምትሰማ 'ጀምዬ' የሚጠራት) 'አልኮል አልጠጣም እኮ እያወቅህ፣ ለስላሳ ይሻለኛል' እያለች እያስቸገረችው፡፡ ልምድ ባለደለደው የፍትወቱ ቅመማ፣ ተገትሮ አድሮ፣ ተገትሮ ያሳደራት፡፡ የሠርጉ ዕለት ውበት፣ ሰንስኖም ቢሆን ትዝታው በልቦናው እስከዛሬ አለ፡፡ እንግዳ በሆነ ስሜትና አስገራሚ ግጥጥሞሽ እዚህ ፊት ለፊቱ አለው ሻገር ሆቴል በር ፊት ለፊት የቆመው ምናልባት ሃያ አመት የሚሆነው ረዥም የተከዘ የመሰለ ፀጉረ ልጩ ወጣት ከሳምንታት በፊት መንገድ ላይ ያየውን የጅማወርቅን ወዳጅ ያስታውሰዋል፡፡ ከጀርባው፣ ለቀስተኛ ወደ እሱ አቅጣጫ ተሰልፎ ሲመጣ ያያል፡፡ ይኼ ደሞ ለሁለት ሳምንታት ያህል አእምሮው ውስጥ እያለሳለሰ የገባውን ምኞቱን ቀሰቀሰበት……

*          *

አንድ ቀን በስራ ብዛት ምክንያት የመሸበት አለቃውን ሆቴሉ አድርሶ፣ መኪናውን መስሪያ ቤቱ መውሰድ ስላልቻለ እግረ መንገዱን፣ (አድርጎ የማያውቀውን) ጅማወርቅ በምትማርበት የማታ ትምህርት ቤት በኩል ትምህርቷን ጨርሳ ስትወጣ ጠብቆ ሊወስዳት ይሄዳል፡፡ እዚያ ሲደርስ ግን፣ ትምህርቱ አልቆ ወደየቤቱ የሚሄደው ተማሪ ትርምስና እነሱንም ለመጫን የተሰለፈው የተሽከርካሪ ብዛት መኪና ማቆሚያ ቦታ ስላሳጣው ተበሳጨ፡፡ ሲባል ቢሰማም የማታ ተማሪ እንዲህ ይበረክታል ብሎ ገምቶ አያውቅም፡፡ ወደ ቤቱ ከሚሄዱ በፊት

የብስጨቱን ትንሽ ፍም ለማቀዝቀዝ፣ እዛው አካባቢ አንድ ቦታ አረፍ ብሎ ማኪያቶ ጠጥቶ ቤቱ ሊገባ ወሰነ::

የሚፈልገውን ባያገኝም፣ በአንድ ሻይ የካፌን አምሮቱን ቆርጦ፣ ቁጣው ሰክኖ ከቡና ቤቱ ወጣ:: መኪናው ውስጥ ገብቶ ድንገት ባገኛት አይነት ወደ ቤቱ ለመሄድ እየነዳ እግረ መንገዱን በትምህርትቤቱ መግቢያ በኩል ሲያልፍ፣ አካባቢው ከተማሪ ጋጋታና ከመኪና ሰልፍ ፀድቶ አጋጠመው:: ያ ሁሉ ትርምስ በምኔው እንደቀለለ በመገረም ራሱን ሲነቀንቅ፣ ከትምህርት ቤቱ ዋና መግቢያ በስተግራ፣ ከመንገድ መብራት የተሸሸገ፣ የዛፍና የግንብ ጨለማ አለበት ቦታ፣ ጅማወርቅን ከአንድ ሰው ጋር ቆማ አያት:: የመኪናውን ጎማዎች በትንሹ ያስጮኸ ፍሬን ያዘ:: ያየውን ካረጋገጠና ሚስቱ መሆንዋን ካመነ በኋላ ወደ እሷ ነድቶ ሊጠራት አሰበ:: ፍሬኑን እየለቀቀ *ለምን የሚሆነው እስኪያልቅ አልጠብቅም?* ብሎ ወሰነ:: ከግማሽ ሰአት በፊት መኪኖች የተገጠገጡበት አንድ ጠርዝ፣ አሁን ግን ባዶ የሆነ ቦታ ላይ፣ ከትምህርት ቤቱ መግቢያ ሳይደርስ ፈቀቅ ብሎ ሞተር ሳያጠፋ ቆመ::

ሲያያት ሁኔታዋ የተዝናና ነው:: ከወገቧ በታች የምትቅለሰለስ ትመስላለች:: ከወገቧ በታች ታረገርጋለች:: የምታረገርገው ከእሱ ጋር ብቻ ነበር:: *ለምን ታህታይ ገላዋ ይቀለሰለሳል?* ትክክል ያልሆነ ነገር እንደተሰማው፣ ጅማ ወርቅ ሁለት እጆቿን ዘርግታ ሰውዬው አንገት ላይ ተጠመጠመች......

*    *

ተኮላ ማነው?

በኡራኤል ክፍለ ከተማ በተለያየ ቅላፄ፣ ዜማና ሰዋሰው 'ያ አጥፊ!' ከተባለ እሱ ተኮላ ነው:: እስከዛሬ ድረስ ወዳጆቹና ጠላቶቹ በጉርምስናው ጊዜ ባወጡለት ቅፅል ይኮራል:: በሁለመናው መሸበት ቢጀምርም ባለፈው ዘመን 'አራዳነቱ' ይፎልላል:: በትምህርቱ ደካማ ይሁን እንጂ ከሰው የመግባባት ችሎታው ከዶክተርነት በላይ ማዕረግ ሊያሰጠው ይችላል:: የአፍ ቀልጣፋነቱ ብቻ ሳይሆን፣ መልክና ቁመናውም ከብዙ ወንዶች ያስመርጡታል:: በአፉም በቁመናውም ፀኒን ወይም ጆሊ ነው:: ዛሬ ለትልቅ ባለስልጣን ሾፌር የሆነው አንዳንዶች እንደሚያወሩት በዘመድ አዝማድ፣ በጎሳና በፖለቲካ ተመርጦ ሳይሆን በቁመናውና በጨዋታው እንደሆነ እሱን የሚያውቁት አውሪዎች ይመሰክራሉ:: አለቃውን መኪና ላይ

ከጫነው ጀምሮ ቤቱ እስኪደርስ ያስቀዋል:: ከሚያመላልሳቸው ከተሜም ይሁን ገጠሬ ያለቃው ወዳጆች እንደ ፀባያቸው ዓይነት ጨዋታ ፈልስፎ መግባባት ስጦታው ነው:: ተኮላ ተደብሮ አያውቅም:: 'ብዙ የሚያስደስት ምናምን ነገር ባለባት አለም ላይ ለምን ብዬ ልደበር' የሚለው ዘዬ አለው፡፡

*እህ* ብለው ከሰሙት ተኮላ የማይለው ነገር የለም:: አንዱ: *ለሴት መጨነቅ አያስፈልግም::* ስለሴቶች ያለው እስከዛሬ ዘመን የሚያምንበት ፍልስፍና ነው:: ምክንያቱም ለተኮላ ሴቶች የሚነኩ ብቻ ነበሩ:: በዘንግ ወይ በከዘራ፣ በመቋሚያ በመሳሰለ:: አዲስአባ ለእሱ አንድ ትልቅ የሴት ቆዳ ናት:: እሱ እንደሚለው ቆዳው በጣም እርግብግብና ለስላሳ ነው:: እሱ እንደሚለው የማይለው የለም እንጂ ይሄ ቆዳ በትንሽ ጨዋታና ቀልድ፣ ኡዞ፣ ጁስና ታላታሊ፣ ቅቅልና ክለብ ሳንድዊች ይቀልጣል:: ንክኪው እንደ እሱ ልማድ ዕድሜው አጭር ነው: *አንዲት የሴት ነጥብ ላይ ተቀስሬ የምከርመው ለምንድነው?* ይላል:: *መክረም ሳይሆን መዋል::* የማይለው የለም:: ከሶስት ወር በፊት ያወጣትን ዛሬ ቢያያት አያውቃትም:: ስማቸው አእምሮው እርጥብ ብራና ላይ በጭስ እንደተፃፈ ሁሉ በአፍታ በሌሎች ሴቶች ትንፋሽ ይገፈፋል:: በአእምሮው ያለው ምስል የቆዳ ብቻ ነው::

አንዳንዴ ሴት አውልነቱ ዝና ሆኖት (ሴቶች ሴት አውል ይወዳሉና) የሚመጡት ሴቶች *እምቢ አንሰጥም* እንዲሉት ሁሉ ይመኛል:: አንዳንዴ በፉክክር ጦርነታቸው *እኔ ከእሷ አንሼ ነው የማታደርገኝ* የመሰለ ግዴታ የጣሉበት ይመስለዋል:: እንዳልገባው ሁሉ በመቀናናት ንቃት የተገነባውን የሴቶችን ጎርፍ ይጋልባል:: ( በነገራችን ላይ እንደተወለደ ግዙፍ ነበር፣ አራት ኪሎ የሚመዝን ባለቃጭል:: *እልልታ* የተባለች ስሚ የተጠራ የሰፈራቸው አዋላጅ አጣጥባ በጀርባው አስተኛችውና ወገቧን ይዛ በመገረም አየችው:: ጎንበስ ብላ ከእግሮቹ መሃል ጉች ያለውን ክብ ነገር በሁለቱም መዳፎቿ ይዛ እንደ ዱባ እያገላበጠች እየመዘነች በምጥ ለተዳከመች እናቱ የሸፈናትን የላብ *መጋረጃ* አሳልፋ *'እትዬ አስናቁ! (ሰፈር 'አስናቁ' ነበር የሚላቸው) ሰሙኝ አስናቁ! ይሄ ልጅዎ ጤነኛ ነው:: ግን ሴት አውል ኮርማ ይሆናል* አለች አሉ) ተኮላ የተወለደው በሁለተኛው የአለም ጦርነት ማለቂያ አሜሪካኖች ናጋሳኪ ከተማ ላይ አቶሚክ ቦምብ ሲጥሉ ነው:: በትክክል አልተነገረም እንጂ አሜሪካኖች የጣሉት

ሶስት ቦንቦች ነው፡፡ ቶኪዮ ላይ እንዲወድቅ የተወረወረው ሶስተኛው በሆነ ተአምር እትዬ አስናቁ ማህፀን ገባ፡፡ አንዳንዳቹ እንደሚሉት እናቱ አስናቁ በትክክል አይኑን ሳያዩት፣ ሳያጠቡትና ሳይስሙት ሕይወታቸው ያለፈው በዚህ ሰበብ ነው ይላሉ፡፡ የኡራኤሎችም ተረት ይሆናል፡፡ ታዲያ በዕድሜው ምሽት አከባቢ በቅርቡ ትዳር ከመያዙ ሁለት አመት ሊሞላው አራት ወር ጉዳይ ላይ ሞቅ ያለው የኡራኤል አዝማሪ እንዲህ አለለት ይባላል፡

*በኒንጃ ስልት ፅንሰት፣ ነፋስ ስልክ ተወልዶ ኡራኤል ያደገው*
*በሰው መውደድ ስልቱ የሚያርበደብደው*
*ሳተናው ተኮላ የጆቴ ልጅ ይኼው*

* *

ይህቺ አሁን ሚስቱ የሆነችወን 'ጅማወርቅ' የተባለች ልጅ ከወደዳት በኋላ፣ ከአልኮል መጠጥ፣ ከሚጨስ ነገር በአጠቃላይ ከ 'አጥፊነቱ' ራቀ፡፡ እኩለ ሌሊት የማያቆማቸው ዟሪ እግሮቹ፣ ፀሐይ ሳትጠልቅ ሚስቱ ዙሪያ መሰብሰብ ጀመሩ፡፡ አባትና እናቱ ሰርቪስ ቤት ተከቶ ከስራ ይሸሽ፣ ስራ ይንቅ፣ *ከፈሱ የተጣላ፣ ፈሱን በጥፊ የመታ* እየተባለ ሲታማ የነበረው ተኮላ፣ ጅማወርቅን ካገባ በሁዋላ *ዘልዛላነቴን ትቼአለሁ* ለማለት ባለው ዕውቀት ሾፌርነት ተቀጠረ፡፡ ሲነዳ ለሚያየው፣ እንደ ሾፌርነት የሚወደው ነገር ያለ አይመስልም፡፡ ይሄን እሱ ያሳየውን ታላቅ ለውጥ፣ የሚያውቁት ኡራኤሎችና የኡራኤል ቅፅል ስም አውጪዎች መቀበል አልቻሉም፡፡

በትምህርት አምኖ አያውቅም፡፡ ለትዳሩ አዳልቶ አንጂ ዛሬም የትምህርት ጥቅሙ ምን እንደሆነ አልደረሰበትም፡፡ ያነበባቸው ሶስት የዛቬራ ሆላንደር የእንግሊዘኛ መፃሕፍት ናቸው፡ *The happy hooker, The happy hooker goes to holywood,* እና *The happy hooker goes to Washington*፡፡ ያውም እየጠጣ ለአራድኛ ወሬ እንዲያመቸው፡፡ በአፍ ልማድ የሚያውቀውን ሰው ሊክብ፣ ወይም የሚያውቀውን የተማረ ሰው በማክበር አስመስሎ በእጅ አዙር ራሱን ለመካብ ይጠቀምበታል እንጂ በትምህርትና በተማረ ሰው አያምንም፡፡ ሰው የሚማረው ጥሩ ለመብላት፣ ጥሩ ለመጠጣት፣ በጥሩ ቤት ለመጠለል ከሆነ ከተኮላ የበለጠ ፕሮፌሰር አለ? ሺህ ቢፈላሰፉ፣ ሺህ መፃፍሕት በፈረንጅኛ ቢያንቸለችሉና ሲሚንቶ እያቦኩ ድንጋይ ቢክቡ፣ ሺህ ሞተር ቢቀጠቅጡ የየትም አገር ስልጣኔ ግብ በሕይወት ኖሮ መደሰት፣

ደስታን ከማንም መሻማትና ይሄን ላለመልቀቅ ወይ ላለመነጠቅ ሰበብ እየፈለጉ መጠፋፋት ነው:: ተኮላ ቆንጆ ሴት እግሮች ሲገባ የሚያሰሙት ድምፅ ከታጅመሃል አያምርም? በቀስታ ከሚከፈት ከሚዘጋው የጅማ ወርቅ አፍ የሚወጡት *'እሰዬዎች' 'ተኮልዬዎች' እና 'የእኔ ተኮላዎች'* ከፒራሚድ ትዕይንቶች አይረቁም? የጅማ ወርቅ ትንንሽ ጡቶችና በለስላሳ ጎፈሬ የተጋረደችው እርጥብ ሕልፅዋ ከመኪና ሞተር አያምሩም? እንደሚለው ቢማር ባይማር አበሻን አርሳው ማንም የሰው ልጅ የትም አይደርስም:: *ዲግሪውን ደረስንበት* ቢሉም ከእሱ የተለየ አልሰሩም:: ይሄ ፍልስፍናው በሚያውቁት ሁሉ የታወቀ ስለሆነ *ለምን አልተማርክም?* የሚለው የለም:: ካነሱበት እሱ እንደሚለው 'ልክ ይነግራል':: *ታዲያ* ግን ከሚጠላቸው ብዙ አይነት ፍጡራን: ከጤይባዎች፣ ከፖለቲከኞች፣ ከደባሪዎች አንዱ ነገር ትምህርት ሰለሆነ፣ ትዳሩን ለማሻሻልና ጅማወርቅም ከእሱ የተሻለ ብሩህ ስለምትመስል፣ *ማታ ማታ* እየከፈለ ያስተምራት ጀመር::

አኗኗሩ የተራ የመንግስት ሾፌር አይመስልም:: የእሱና የጅማወርቅ መተዳደሪያ ሜኑ በሜኑ የሚመጣው ከደመወዙ ስላልሆነ ነው:: አባቱ እንዳይቸግረው በማለት ከሚያከራዩአቸው ጥቂት ቤቶች የአንዱን ለትዳሩ መደገፊያ መድበውለታል:: ትዳር መስራቾችና የእነሱ አጨብጫቢዎች እንደሚሉት *የተሟላ ቤት* አለው:: አጥሩ የሲሚንቶ የግንብና የሸክላ ሚስቶ ነው:: በሩ ብረታብረት ነው:: ግቢው ጫታ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ቀለማት ባላቸው አበቦችና የፅድ ዛፎች ሐመልማል የታተመ ነው:: ጠዋት ጠዋት እሁድ ጅማ ወርቅ ተፈጥሮ አድናቂ ናትና ጋቢ ተከናንባ፣ ወዲያ ወዲህ እያለች ፀሐይ እየሞቀች አበቦችን እየነካካች ስታሰላስል፣ ልጅነቷ የበለጠ ሲወጣ ያያል:: *ጉግስ የሚያጫውት አልጋ* እሱ አንደሚለው (ፈረስ ጋልቦ ባያውቅም) የተዘረጋበት መኝታ ቤት፣ ፒያሳ ባንኮ ዲሮማ ጀርባ ናፖሊ የተባለ ጣሊያን የሰራው ሳሎኑን የሞላው ሶፋ አለው:: (ራቱን በልቶና ጠጥቶ የልቡ ደርሶ ጋለል ብሎ ሲቀመጥ ሙሶሎኒን የሆነ ይመስለዋል:: በዚህም ብቻውን ይስቃል::) ከሶፋዎቹ ፊት ለፊት 32 ኢንች ሶኒ ቲቪ፣ የሙዚቃ ካሴት ማጫወቻ ሶስት ርብራብ የፊሊፕስ ዴክ እና አሁን አሁን መጣ የተባለው ዲቪዲ ማጫወቻ፣ በእርጅና የወለሉ ሸክላ መሰንጠቅ የጀመረ ቢሆንም ስፋቱ ሁለት ጥንድ ባልና ሚስት

ሊያላፉ የሚችል ባኞ ቤትና መታጠቢያ ቤት አለው:: ከዚህ ባኞ ውጭ ቆሞ ወይም በነጠላ ጫማ ወዲያ ወዲህ እያለ ጅማ ወርቅ ስትተጣጠብ ማዳመጥ ይወዳል:: በር በቀስታ ከፍቶ ገብቶ መጋረጃ ገልጦ ሲያስደነግጣት......*ውይ ያስደንግጥህ እቴ!* ብላ እንዳፈረችው ሁሉ ገላዋን ስትሸፍን እና ውሃ የወረደበት እርጥበቷ በውበቱ ሲያስገርመው (ፊቷ ላይ የተጣበቀው ዞማና ትኩስ ውሃ ያቆማቸው የጡቶቿ ፍንጮች):: የሆዱ ነገር ሆዱን ይቆርጠዋልና ከሁሉ ደስ የሚለው ከማድቤት የሚመጣው የተለያየ አይነት የሚያምር ጠረን ነው:: ጅማ ወርቅ ሙያ አላት:: እሱ እንደሚለው *እንደማንም ወንድ ሆዴን እወዳለሁ::* ጋለል ብሎ ከማድ ቤት የሚመጣውን መአዛ ሳሎን ሆኖ ሲሰነፍጥ ላቱ ድረስ በደስታ ይርገበገባል:: አይኖቹን ጨፍኖ ምን ምግብ ተሰርቶ እንደሆነ መገመት ከማንም የማይጋራው የጠረን ጨዋታው ነው:: ሆዳም መባል ግን አይወድም:: ከክርስቶስ ታምራቶች ሶስት አራቱ ሆድ ጠቀስ ሳይሆኑ አይቀሩም፣ ግን ያፍራል::


ጥቁር ቆዳ ጫማዎቹ ሁልጊዜ አንደተጠረጉ ነው:: በንፅሕናቸው ስለሚተማመን ሳያወልቃቸው ሶፋ መደገፊያ ላይ እግሮቹን ዘርግቶ የጫፎቻቸውን አሿሿል፣ የሲሮቹንና የቆዳቸውን የቀለም ተግባቦት፣ የሸዋ ጫማ ቤትን ኪነጥበብ እያደነቀ፣ ጥቁረታቸውንና እንቅፋት አብሯቸው የተገነባ የአዲስአባ መንገዶች ያነቆሩትን የነጡ ጠባሶች እየታዘበ፣ ሆዱን እየዳበሰ *ጀምዬ! ሰማሽ?! ጀምዬ ራት ምን አለ? ምን የሚበላ አለ ዛሬ?* ሲል በትክክል አባወራ እንደ ሆነ ይሰማዋል::

*ተክዬ፣ ተኩ፣ ተክሸ፣* (በጅማ ወርቅ አባባሎች) በዚያም በዚህም ብሎ ደህና ኑሮ ይኖራል:: የሚያብለጨልጭ ወዛም ገፁ፣ ያበጠው ጉንጩ፣ ስጋ የሞላው ቁመናውና ቀና ብሎ አካሄዱ ተኮላ እንደተመቸው ይመሰክራሉ::

የድሮ ስሙ ግን አሁንም አብሮት አለ:: አሁንም ሊኮራበት ይፈልጋል:: ላይኮራበትም ይፈልጋል:: አሁን አሁን ስሙ ትርጉም ያለው አይመስለውም:: ደሞ ይሟከለዋል፡፡

ተኮላ ጅማወርቅን ካፈቀረ በኋላ 'ፍቅር ደካማ ጎን አለው' በሚባለው ነገር ማመን አቁሞ ነበር:: ግን ዘመን ዘመን አለው ፍቅር ደካማ ጎን ያለው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ ራሱ ደካማነት የሚሆንበት::

* *




ፈዞ ከቆመበት ባኖ ተቃቅፈው ወደ ቆሙት ሰዎች ለመቅረብ ሲያስብ ጅማወርቅ እጅዋን ሰዳ የሰውዬውን እጅ ስትነካው አየ:: ከዛ ደግማ በቀስታ ተስባ እጆቿን ግራና ቀኝ ዘርግታ አንገቱን አቀፈችው:: ያኔ ሆዱ ውስጥ የሆነ ነገር ፈርጦ የፈሰሰ መሰለው:: እንዲህ ታደርግ ነበረ:: እሱ ከተቀመጠበት ሶፋ በአፉ እያንቆለጳጰሰ ሲጠቅሳት፣ *ጆምዬ/ ጆምንት/ የእኔ ዞማ/ ስዊት ቤቢ/ ጂጂዬ/ ጂሚዬ/* ከቆመችበት ወደ እሱ እጆችዋን ግራና ቀኝ ዘርግታ ትመጣለች:: እሺታዋ ውስጥ ያለው ገና ያልረገፈ የልጅ መግደርደር፣ ሁለመናውን እንደ ስልክ እንጨት ያቆመዋል(እንዲህ ያስባል):: ወደ እሱ በቀስታ ጎትቶ እግሮቿን ግራና ቀኝ አንስቶ ዳሌው ላይ ሲያስቀምጣት፣ ቀኝ እጅዋ አያቅፈውም ነበር:: አየር ላይ እንደዛ ትምህርትቤቷ በራፍ ላይ ሰውዬውን ለመንካት እንደዘረጋችው ዐይነት ይንሳፈፋል:: ይሄን ሲያስብ አጠገባቸው የነበረ (የእነሱ ያልመሰለው) አንድ መኪና ውስጥ ሁለቱም ተከታትለው ሲገቡ አያቸው:: ሆዱ ላላ:: አናቱን ዞር አደረገው:: መሪው ላይ ግንባሩን ሲያስደግፍ ፈሱ አመለጠው::

መስኮቱ ተዘግቶ ለስ ያለ ፀጥታ በነገሰበት መኪናው ውስጥ ይህቺን ፈስ ሲፈሳ እንግዳ ስሜት ተሰማው:: ከፈሳ ብዙ ጊዜው እንደሆነው ተገለፀለት:: ሊፀዳዳ ሽንት ቤት ሲገባ ካልሆነ በስተቀር እንዲህ በባዶ ሜዳ ፈስቶ አያውቅም:: በዕድሜው መግፋት ስቡ እየታለበ ጠፍጣፋ ከሆነው፣ ምን እንደሚመስል እንኳን ዞር ብሎ አይቶት ከማያውቀው መቀመጫው (እንደ ፀጉር አይበጠር፣ እንደ አይን አይቀነደብ) በመፍሳቱ ብቻ ደንግጦ አልነበረም:: የፈሱ ድምፅ ከሰው አንደበት የወጣች መምሰሏም ነው:: የሆነች እንስትነት አላት:: የሆነ ድሮ የሚያውቃት በትንሹ የረሳት ሴት ድምፅ:: የሰፈሩ ልጅ ገነት ትዝ አለችው:: እዛ አራት ኪሎ አለማየሁ ሱቅ የማትጠፋ:: ፈሷ እንደ እሷ ረጋ ያለች ትመስልና ልታልቅ ስትል ግን ፈጠን ቆጣ ትላለች እንደ አጭር እግረ ቀጭን ነገረኛ ሴት (እንደ ስላስ)::

እንደገናም ይህቺ ምላስ አልባ ልሳን፣ ይህቺ እንጥል አልባ አንደበት፣ ከራሱ መቀመጫ የወጣች አልመሰለውም:: ግን እንዴት ሁለቱ ማለት መውጣትና አለመውጣት ሊሆን ይችላል? እንዴት

ረጋ ያለች ገነትና ነገረኛ ስላስ አንድ ይሆናሉ? ሌላው ያስገረመው ጉዳይ የፈሱን ቅላዔ እየተነተነ እያለ መጥፎ ጠረን አፍንጫው አለመድረሱ ነው፡፡


ሚስቱ የገባችበትን መኪና እየተከተለና በፈሱ ጠረን-ጠቢስነት እየተደመመ እያለ መስኮት ከፈተ፡፡ በዚህ ተራ ጉዳይ ተበሳጨቶ ትኩረቱ ሲበላሽ፣ በእሱና ጅማወርቅ በተሳፈረችበት የቤት መኪና መሃል አራት ተሽከርካሪዎች ስለተሰነቀሩ የፈለገውን ያህል ሊጠጋቸው አልቻለም፡፡ ቢሆንለት፣ መንገዱ ሰፋ ቢል፣ በሚያውቅበት ቅልጥፍና ከፊት ለፊታቸው አቁሞ፣ ከመኪናቸው አስወርዶ፣ ጅማወርቅን በቃሪያ ጥፊ፣ ያቀፈችውን ሰውዬ በኡራኤልኛ ብሩስ ሊ፣ የሚሾፍራቸውን አቃጣሪ በቴስታ ይላቸው ነበር፡፡ እድሜው ለዚህ አይነት የጥል ዝባዝንኬ ባይመችም፣ ከራሱ ለተጣላ የዘመኑ ሂፕ ሆፕ ውጫጩ፣ የአሜሪካ ዲቪ ማስቲካ ልቦናቸው ላይ ለተጣበቀ፣ በራሳቸው ከመሰልጠን ይልቅ ወደ ሰለጠነው ለመሰደድ አግራቸውን ለሚያሳክካቸው፣ አንጎላቸው ጠማማ ጥበብ ለተሞላ አያንስም፡፡ ስደት፣ ስደተኛና ጩብጥ ይጠላል፡፡ *ምን ጎደለብኝና?*

ራስ ምታት ጀመረው፡፡ እርስ በራሱ የሚጋጭ ነገር ሲያስብ ሁልጊዜም እንዲህ ይሆናል፡፡ ያሳደገውና እሱ ብቻ የሚያውቀው አብሮት የተወለደ ለጅማወርቅ እንኳን ያልነገራት ራስ ምታት ነው፡፡ ያኔ በጎረምሳነቱ፡ ራስ ምታቱ ሲነሳ፣ ስልክ አንስቶ የሚያውቃት አንድዋ ቆንጆ ጋ ይደውል ነበር፡፡ ከዛ እርጅና ጭጭ ያደረገው የአባቱና የእናቱ ግቢ ሴንጢ በማለ የኮረዳ ቅትቻ ይዘነተራል፡፡ በፀጉራቸው አሻሽተው፣ ወዛቸውን እንደ ካፍሽሮፕ ግተውት፣ ሳምንት ታሽጎ የቆየ ዘሩን አርከፍክፎ የልቡ ሲደርስ ተመልሶ ይተኛል፡፡ የዛን ጊዜ ንግሥት ዘውዲቱውም ፋርማሲውም 'ዶናዎች'[2] ነበሩ፡፡ ይሄ ተወልዶ ያደገበት ራስ ምታቱ የተወው ጅማወርቅን ካገባት ጀምሮ ነው፡፡ ስለራስ ምታቱ ታሪክ ለጅማወርቅ ምን ብሎ ይነግራታል? ሲጋጭብኝ ራሴን ያመኛል? 'ምን ከምን ሲጋጭ' ብትለውስ?

ከድሮም ይደብቃል እንጂ ብዙ ነገር ይጋጭበታል፡፡ ድሮ የሚጋጭበት፡ *አልማዝ ትሻላለች ንግስት? ንግስት ደስ የሚል ጡት አላት ስትስቅ ደስ ትላለች፤ ያቺ እንትና ግን እንትኗ ደስ ይላል ግን ፍንጭት ናት፣ ደሞ ያቺ አለሚ ሁዋላዋ ያምራል......ሱፐር ስትራክቸሯ ይከይፋል ምናምን፣ ያቺ ፀደይ ግን......*በቃ ይሄ ያዞርበታል፡፡ የሚያዳላው ግን ለሰልካካ ፊት ነው፡፡ ይቆይና እንትናን ከአለሚ

አብልጦ ስለመረጣት ይቆጨዋል፣ ይሄም የራስ ምታቱ ሰበብ ነው:: ቅንጡንና ግንባሩን እያሸ፣ እየተራገመ፣ ሚስቱ የገባችበትን መኪና መከተሉን ቀጠለ:: አንድ መስቀለኛ ቦታ ሲደርስ የት እንደሄዱ ጠፉበት:: በደብዛዛ ጨለማ ውስጥ አይኖቹ እስኪፈርጡ ቢያፈጥ፣ በቀስታ እየነዳ ወዲያ ወዲህ እየተመላለሰ በፈልግ፣ ሊያገኛቸው አልቻለም:: መኪናውን ወደ ዳር አውጥቶ አቆመና መሪውን በሁለቱም እጆቹ አንድ አራቴ ደበደበ:: ለአራተኛ ጊዜ የሰነዘረው የግራ እጁ ቡጢ መሪውን ከመንካቱ በፊት ለሁለተኛ ጊዜ ላጥ አደረገ:: ትልቅ ስህተት እንደሰራ ሁሉ ጎንበስ ብሎ ግንባሩን መሪው ላይ ደፍቶ አዳመጠ:: አልተደገመም::

የዚህችኛዋ ፊሱ ድምፅ ዝግ ያለች ትፈሳ አትፈሳ የምታምታታ ነበረች::




ለተኮላ መከሰቷና አለመከሰቷ ግልፅ ያልሆነው፣ ያለ ተከታይ ያለ አጃቢ ያለ ሚዜ በመምጣቷ ነው:: ዝግ ብትል ዘረጥ ትሆን ነበር:: ምናልባት ዘረጥ የውስጥ ባህርይዋ (ወርቅ) ሲሆን ላጥ ያስመሰላት በጊዜ የተከሰተችበት እሱ ያዳመጠው ፈጣን ቅርፅዋ ነው(ሰም):: በመፍጠንዋ ግርማ ባይኖራትም፣ እርጋታዋ ኩታቸውን አናታቸው ጣል አድርገው ኩርሲ ላይ የተጎለቱ፣ በከፊል በዕጣን ጢስ የተጋረዱ፣ *ቤቴ ይሄ ነው ግን አንድ ሰራተኛ ብቻ ነው ያለችኝ* ብለው የሚያማርሩ ፊተ-ክብ፣ ከንፈረ-ስስ፣ ደልዳላ ፊውዳል ሴትዮ ናት:: ላጥ አንድ ቦታ መርጋት ያቆመች በሰባት አመታት ውስጥ ሶስት ባል አግብታ የፈታች ዛሬም ወንድ አይነአዋጅ የሆነባት ሀበባሊ[3] ናት:: ተባዕት ትሁን ብንል ዘረጥ ቀርፋፋ ሰጋር በቅሎ እንደ አህያ የሚጋልብ ባላምባራስ ነው:: ወይ ሲናገር አ አ አ አ አ የሚያበዛ ባለስልጣን:: ላጥ የሰለቸ ግልብ ነገር አቀላጥፋ የምትናገር ሴት ካድሬ ናት:: የፊስ ስክዞፌርንያ::

ተኮላ በቀስታ እየነዳ ጠረን በአፍንጫው ሰለለ:: አልሸተተውም::

እንግዳ በሆነ መልክ በብዛት ስላባበው በብስጭት ኮቱን አውልቆ ወደ ኋላ ወረወረና በግንባሩ አንድ ሶስቴ መሪውን ተመተመ: ምን እንደሚያስብና ምን በማሰብ ላይ እንዳለ ግልፅ አልሆነለትም:: ቀና አለና *'ምን ሆንኩ?'* አለ ለራሱ:: *'ምን አጠራጠረኝ?'* መኪናውን ባለመደው አቅጣጫ በፒስታ መንገድ ላይ

እየነዳ፣ እየነጠረ፣ ጥርሱን እየነከሰ ኡራኤል ገባ:: ቤቱ ፊት ለፊት ሲቆም፣ በሕይወቱ ተሰምቶት ያማያውቅ ቁጣ ከውስጡ መምገል ጀመረ:: ይኼ ቁጣ ገላውን ከላይና ከውስጥ የሚያነድ ብቻ ሳይሆን፣ የሚያጅበውን ትምክህተኛ መንፈስ የሚኅነትል፣ ዝቅተኛነትን የሚቀሰቅስ ህልዮ ሆኖ ነው::

ተኮላ ሳይፈልግና ፈቃድ ሳይሰጥ *የእሱ የሆነች ሴት* ለሌላ ወንድ ትታው ሄዳ አታውቅም:: ባለስንት ሕብረቀለም 'ማስደገፍ' አለው በትዝታ ባንኩ? እሱ ያወጣቸው ግን ከመጤፍ ያልቆጠራቸው ሴቶች በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ እሱ አንዳወጣቸው ለመናገር ሲታክቱና አድማጭ ሲለማመኑ ሰምቷል:: በልጅነታቸው የትዝታ እርሻ ውስጥ ተተክሎ፣ ትዳራቸውን በተራዘመ ውድድር ውስጥ እየከተቱ በስተርጅና ራሳቸውን እንዲጠሉ ያደረጋቸው ጥቂት አይደሉም:: ይሄ ሁሉ 'ትልቅነቱ' ጅማወርቅን በመውደዱ እየተናደ መሰለው::

ከመኪና ሳይወጣ ቤቱን ከውጭ እያየ ለሩብ ሰአት ያህል ቆመ:: ሊገባ አልፈለገም:: እናም፣ ሆኖ የማያውቀውን ቢራ ጠማው:: ከስንት ወራት በኋላ ቢራ ጠማው:: ከአንጀቱ፣ ከደም ስሩ እንደ ኅረምሳነቱ ጊዜ ቢራ ጠማው:: አፉ ደረቀ:: ከመስከር ለማምለጥ ጥማቱን ችላ ብሎ ቤቱ ሳይገባ ነዳጅ እስኪያልቅ ድረስ በመቶ ሃያ ወደ ኮተቤ አቅጣጫ መንዳት ፈለገ:: አላደረገውም:: ወደ ኋላ ዞሮ እዛው ሰፈሩ አንድ ቡና ቤት ገብቶ ቢራ አዘዘና አየሩ ወጥቶ ያለቀ ፊኛ መስሎ ተቀመጠ......

ምን ያህል ጊዜ ቡና ቤቱ ውስጥ እንደቆየ፣ ስንት ቢራ እንደጠጣ ትዝ አይለውም:: የድሮ ዘፈኖች ቡና ቤቱን ያደነቁራሉ:: የአየለ ማሞ በማንዶሊን የሚጫወታት *ጠይም አሳ መሳይ በውበት ያጌጠች* ይንኮራኮራል:: ይሄን ዘፈን ድሮ ግዮን ሆቴል ቦውሊንግ እየተጫወተ ሜታ ቢራ እየመጠጠ ይሰማው ነበር:: በከፊል ልቡ ዘፈኑ ጋ ቆየ:: ያ ሁሉ ዘመን አልፎ በዚህ ሰአት እዚህ ቦታ እንደሚደርስ ከእግዜር ሌላ ማን ያውቃል? እሱን ትቶ ስለሚስቱ ማሰቡን ቀጠለ:: ከተዋወቁበት ጊዜ ጀምሮ ከጅማወርቅ ጋር ሲያደርጉት የነበረው ትንንሽ ጉዳይ ሁሉ...... እንደተንቀሳቃሽ ፎቶዎች ሳውንድ ትራክ የገባላቸው....../*በእናትህ ቁርስ ቅመስ/ ምን ሆነ አይንሽ ቀላብኝ አልተኛሽም?/ እማማ ደውላ ሰላም ብልሃለች/ ሆዴን ይቆርጠኛል አፈር ስሆን ሳምልኝ/ ቀስ በል ምነው እስከዚህ የትም አልሄድብህም/ ጀርባዬን እሸኝ/ ሲመጣብህ ምልክት ስጠኝ አለ*

*አይደለ ዘፈን ነገር ዝፈን፣ ባለጋሪው የተባለውን ሂሂሀሃሃ አንተ ስድ ባለጌ አደረከኝ/* ስትሆንለትና ሲሆንላት የነበረው ሁሉ ትዝ እያለው፣ ከጥቂት ሰአታት በፊት ስላጋጠመው ክህደት ሊነግረው የሚችል፣ ቀድሞ ልብ ያላለውን ፍንጭ ፍለጋ በሃሳብ እየኳተነ ሲፈልግ፣ ሊያገኝ ባለመቻሉ ከተቀመጠበት ተነሳ:: መስከር ጀምሯል:: በግራና በቀኙ ሚስቱን የሚያስንቁ ብዙ ቆነጃጅትና ወይዛዝርት፣ በኤች አይቪ የሚንቦገቦጉ……አይኖቻቸው እንደ ቅዱሳን ትልልቅ የሆኑ፣ ቀለማቸውም የባቄላ አበባ የመሰለ፣ ራሱ ያሳዝነዋል ከነዚህም ከጅማም አለመሆኑ……ሳይቆምበት የቆመበት በመሰለ ደላይ አፋቸው እነዚህ 'ደህና እደር' ሲሉት አልሰማቸውም::

ከቡና ቤቱ ሲወጣ የድንጋይ ደረጃውን ወርዶ ጨርሶ ቀኝ እግሩ ገና መሬት ሲረግጥ ከአረማመዱ ይሆን ከአወራረዱ ወይም ከሴቶቹ የአንድዋ የሚያምረው ፈጠጣዋ ልቡን ነስቶት፣ እና እሷም ፊቱ ላይ ባየችው ቸልታ በሽቃ በልቧ ረግማው፣ ብቻ ባልገባው ምክንያት ለሶስተኛ ጊዜ ፊሱን ለቀቀ……




በድንጋጤ ወደ ጀርባው ዞር ብሎ አየ:: ማንም የለም:: የድሮ ዘፋኝ 'ቀን አላለፈብኝም' አይነት የዜማ ጋቢ ለብሶ በምሽቱ አየር ውስጥ እንደ ከሴ ጠረን ይሳባል:: በደረጃው ላይ እንደ አስር ሳንቲም ብርዝ ይፈሳል:: በግማሽ አንጎሉ ማንዶሊን እየሰማ፣ በግማሽ አንጎሉ ሬቡን ለመሰብሰብና የፈሱን ሐዲድ ለመስበር ጣረ:: እንዲህም እየለፋ *ምን ሆንኩኝ?* አለ ለራሱ::


ከሆቴሉ ፈቀቅ ብሎ ወደ ቆመችው መኪናው እየተጠጋ ስለፈሱ እርዝመት፣ ከሲታነትና ጠለል አሰበ:: የሆነ ሊቀበለው ያልፈለገ አይነት ውበት አላት:: የሆነች ዶልቼ ሶቶ:: ዙሪያዋ በእቅድ የተከረከመ ዘረጥ:: ጥለት ያላት ደዝ:: በአይነ ሕሊናው የመጡት ሁለት ጉዳዮች ናቸው:: በልጅነቱ ሲጫወትበት የነበረው ሜዳና ጡተ ደቃቃዋ (ቢፈልጓቸው ቢያስፈልጓቸው የማይገኙ)፣ ቂጠ ጠፍጣፋዋ ረዠምዋ ግርማዊት:: ዛሬ ቡና ነጋዴ አግብታ፣ ቡና ገበያ የምትሰራ፣ የቡና ቡድን ደጋፊ::

ባለገንዘብ እፍእፍ ኮሌጅ:: ያም በልጅነቱ እየተጫወተ ያደገበት ሜዳ ዛሬ ለኢንቨስተር እየተቸበቸበ የቻይና ጫማ የመሰሉ ቤቶች የተሰሩበት ለምን ትዝ እንዳለው አይገባውም::


ከዚህ ሁሉ ጋር ለራሱ በትንሹ ፈገግ ያደረገውን ነገር አሰበ፡ *አንድ አይነት እህል ከገባበት ሆድ አንድ አይነት ሬብ ይገኔ በአጭር ጊዜ የተለያየ አይነት ቅላፄ ያላቸው የአይነ ምድር ወላፈኖች ይወጣኛል?*

ነፋስ የሚቀበል እየመሰለ፣ ድንጋይ በእግሩ እየመታ፣ አፈርና ጠጠር በጫማ አፍንጫው እየማሰ፣ አሰበ:: መንገድ ዳር መኪናውን ተደግፎ ቆሞ አይኖቹን በቀስታ እየከደነና እየከፈተ መረጋጋት እንዳለበት ለራሱ ነገረ:: በሚወዳት ልጅ፣ በሚወዳት ሚስቱ እንደተከዳ ቀልቡ ብትነግረውም፤ እንዳልተረበሸ ማሳየት እንዳለበት ወሰነ:: ፊቱም ላይ ይሁን የሚናገራቸው ቃላቶች ውስጥ የመደናገጡ ማህተም እንዳይቀር መልፋት ብቻ ሳይሆን፣ ከነገ ጀምሮ፤ ስልቱ የረቀቀ አከራካሪ መደምደሚያ የማይወልድ የስለላ መረብ መዘርጋት እንደሚያስፈልገው አመነ:: ይሄ ዕቅዱን እየደጋገመ ሲያወጣና ሲያወርድ፣ ከ ‘የመናቅ’ የስሜት አረንቋው እየተጎተተ ወጣና ሁለመናው ተረጋጋ:: የመኪናውን በር ከፍቶ ከጀርባ ኮቱን አንስቶ ለበሰና ወደ ቤቱ ለመሄድ መኪና ውስጥ ገባ:: መንገደኛው ብዙ ነው:: እውጭ እየተጓዙ የሚያድሩ ሰዎች ያሉ ይመስላል:: የመኪናው ሞተር ይንዛዛል:: ፍሪሲዮኒ ረግጦ ማርሽ ሲያስገባ፣ አንድ እስከ አንጀቱ የተሰማው ተስፋ ያስቀረጠው ነገር ተከሰተ:: ሁሉ ነገር ታሽጎ ከነበረ እርግማን ወይም በቅርብ ከተጠነሰሰ የጥንቆላ ውጤት የመጣም መሰለው:: ወይም በከተማው አዲስ በሽታ ገብቷል::

ወንበሩ ላይ ተረጋግቶ ፍሪሲዮኑን ረግጦ ማርሽ ለማስገባት ቀላል ምጥ ሲያምጥ በቂጡና በወንበሩ መሃል ባለው ክፍተት፣ በነፋስ እንደተመታ የባሕር ጠለል የሚርገበገብ፣ ነፋስ እንደ መታው ቅጠል የሚንሿሿ፣ እየተገላመጠም ይሆን እየቋጠረ ሊያስቆመው ያልቻለ፣ የመኪናውን ሞተር ያስነሳበትን ቁልፍ መያዣ ቆዳ ያርገበገበ፣ የሆነ ቀላል የፈስ ሌል ኒኛ አንዛረረ……



ፊቱን በሁለቱም እጆቹ ሸፍኖ ይሳቅ ያልቅስ የሚያደርገው ጠፍቶት በዝምታ ተቀመጠ:: ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ይሄ ሀፍረቱ፣ ይሄ እንቆቅልሹ እንዳያስደነግጠው፣ አንደኛውኑ ሊገላገል፡ የሚችለውን አማጠ:: ሊቆጥራቸው ያልቻለ እንደ ሰንሰለት የተያያዙ ከመሃላቸው ደካማ ሰከንዳዊ እረፍት ያስገቡ ጡጡችና ቁቆች፣ ፓራሞችና ዘረጦች እያከታተለ ለቀቀ::




በትክክል ምንነቷን ሳይስት ሙሉ ለሙሉ የሰማት የመጨረሻዋን ነው:: ገለል ያለች ናት:: መኪናው ጋቢና እግሮቹ ስር ተንጋላ ነፋስ የምትቀበል የአምባ ልጅ:: ቀድመዋት የሄዱትን የናቀች አይነት:: ተኮላ ማማጡ ትርፍ ማምጣት ሲያቆምና ሆዱ ከአየር የፀዳ አንደሆነ ሲሰማው ለራሱ ፈገግ ብሎ (በራሱ መሳቅ የሚችል አራዳ ነውና) መስኮት ከፈተ::

ጥያቄ መጠየቅ ግን አላቆመም:: *ምን በላሁ? ምን የተለየ ነገር በላሁ?* ከዛሬ ማታ እስከትናንት ጠዋት በሃሳቡ ምን እንደ በላ ሊያስታወስ ሞከረ:: *የፈሰ ወረርሽኝ በአገሪቱ ገባ?* እስከ አሁን ድረስ የፈሳቸው ሁሉ በአንድ ተርታ ቢሰደሩ ስርአት ቢሰጣቸውና ድርሰት ቢሆኑ ጥሩ ዘፈን ሊወጣቸው እንደሚችል ገመተ:: አራዳ ነውና በዚህም ለራሱ ፈገግ አለ::

መሪው ላይ ደገፍ ብሎ ከቆመበት አሁኑኑ መሄድ እንደፈለገ ሁሉ መንገድ ይማትራል:: ጨለማውን፣ የጨለማውን ጌቶችና እመቤቶች ያያል:: እዛ የደረቷ ቆዳ ከጎን አጥንቷ በኤች አይ ቪ የተሰፋ:: የመያድ ጠይም ነት፡ ሱፍ የመሰለ ደረት ላይ እንደ ንቅሳት የምትጣፍ:: እንደ ሆነላት ሁሉ የጠላቷን ፍስ እንደ ጠበል የምትቀበል:: እዛ ከምሽቱ የጠየመ ጎረምሳ:: ፊቱ መሃል የትንባሆ ፍሬቻ:: ለምቦጩ በምርቃና ያበጠ፡ በተስፋ መቁረጥ የተሳመ:: አለውና እንደ ዘመዶቹ የመጥፋት ታለንት:: ጫት ቄራ በደነዘዘ መዋሰብ የብዙ ልጃገረዶችን አይኖች አይቷል፡ ካነፈዛቸው እንቅልፍ ሳይወጡ ዘንጉን ሰይለቁ እንደ ተዋሲት የሚሆኑት......የምሽቱ ቂልነት፣ ቀላልነት ቀሊልነት፣ ደሞ አዝናኝነት:: የጥፋት ውበት:: በትንሹ እዛ ነበር:: ስላፈቀረና አፍቅሮም ስለተሸወደ ብቻ ትቶት ወደ መጣው አጥፊ አለም መሄድ አይፈልግም:: እዛ መሄጃም አቅም የለውም::

ብዙ ዘመን አብረው የመኖር ተስፋ የሰጡትን የደስ ደስ ያላቸውን ልጃገረዶች ቸል ብሎ አመት ሳይሞላው ከምተከዳው ተያያዘ:: ጡር ይሆን?

ያቺ ሃና ዛሬ ሁለት የወለደች እና አርሴማ ዛሬ አካውንታንት ሆና ኢንሹራንስ የምትሰራ የት ደረሰች? የት ደረሱ? ያቺ አልማዝ እንደ እሷ ያማሩ እጆች ያላት ማን ናት? አፀደስ? አፀደ ጥርስ መልካም ያለ ኮካ የማትጠጣ……ሃና……አ ሃና……

መኪናው ውስጥ ተቀምጦ መንገደኛ ላይ ማፍጠጥ አደከመው:: በሁለመናው ትኩስ አየር ለመሰብሰብ ሞተር አጥፍቶ ከመኪናው ሊወርድ በር ለመክፈት እጁን ሲሰድ በእሱ በኩል ያለው መስኮት ተንኳኳ:: ቀና ሲል በፀጉር ነዶ የተከበበ የቤላ ፊት እየሳቀ ያየዋል::

* *

--ሰላም ቤላ! ቤልነት! ታዲያስ! አለ

ቅር ያለው ወይም ተጀምሮ ያልተጠናቀቀ ፈገግታ ፊቱ ላይ ነበር::

--ምነው ጠፋህ? ፊቷን በመኪናው መስኮት ገባ አደረገችና

--ምን ደብቀሃል እዛ? አለችው ዞማ ቸብቸቦዋን ወደ ሁዋላ በድንገት እየነጠቀች

--ሃሃ

ነይ ግቢ ሊላት ዳዳው:: የሚያዋራው ሰው ፈለገ:: ከሰው ጋር የመሆን አምሮቱ ተቀሰቀሰበት::

--አንተ በወሬ ሰማሁ ሚስት እንዳገባህ:: ሰርግ እንዴት አልጠራኸኝም? ደሞ ማግባትህን ልታስመሰክር ነው ጉንጭሽን እንኩዋን ልሳምሽ እንኩዋን ያላልከው

--አልወጣኝም በምላስ ሰላምታ አጣደፍሽኝ እኮ

ከመኪናው ወጣና እየተሳሳቁ ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ፣ እጇን ይዞ በፈገግታ እየተፈለቀቀ::

--ትዝ ትይኛለሽ::

እንዲህ ያስባለው ዛሬ ልቡ ያደረው ብቸኝነቱ ነው:: ይሄን ያውቃል ግን ከድሮ ወዳጁ ካቀራረበው ምናለበት ውሸት ቢዋሽ:: ከደረቷ እንደምታርቀው ሁሉ ገፋ አደረገችውና

--ተው እባክህ አለች ድለላ እንደሆነ ያልገባት መስላ--ትንሽ ልጅ ሚስት አድርገህ አረፍከው:: ሰማሁ:: ወሬ አይደበቅ:: ደረቅ:: አለችው በዝነኛ ሳቅዋ ታጅባ::

አንገቷ ዙርያ ሰማያዊ ዘንዶ የመሰለ ስካርፍ ተጠቅልሏል:: እግሮቿ መሬት ሲደርሱ ሲሉ ለመግጠም ስለሚቸኩሉ ሽብልቅ ትመስላለች:: ቂጥዋና ወገቧ እኩል ሰፊ ነው:: ግራና ቀኝ ጫፎቹ ወደ ፊት የገፉ የተቀነፈ የመሰለ ትከሻ አላት:: እዚህ ትከሻ ላይ ፀጉሯ እንደ ፏፏቴ ያደርገዋል:: ይሄን ፀጉር አንደሚያመቻች ሁሉ ግራና ቀኝ ነሰነሰች:: ጎራዳ ቤላ መሳቅ ትችላለች:: *መልክ ባይኖራት ስቃ ማደሪያ አታጣም* ይሉዋት ነበር:: እድሜዋ ከፍ እያለ ሲሄድ ሳቋን እንደ ሃሳብ መጠቀም ጀመረች:: ሲብራራ የሳቅዋን ቅላፄ ከዚያም ጋር ስትጫወትና ስትስቅ የምታነቃንቀውን የገላዋን ከፍል እንደ ሁኔታዎች ማዘዝ ትችላለች ማለት ነው:: ሰዎች ምን እንደምታስብ ቢጠየቁ በትክክል አይገባቸውም:: ግን *ጥሩ ልጅ ናት፣ ተጫዋች ናት* ይላሉ:: ተኮላም የሚያውቃት በተጫዋችነቷ ነው::

* *

ድሮ ድሮ ተኮላ የማረካት ባዶ ቦታ በመስፈሩ ነው:: ለእሱ ፖለቲካ የሚባል ነገር ምድር ላይ የለም:: ሁሉም ሰዎች እኩል ናቸው:: የትኞቹም ሰዎች ስልጣን ቢያገኙ ለእሱ የሚደርሰው ማንኪያ የሚሞላ ሾርባ የለም:: አሸናፊና ተሸናፊ ሺህ ጊዜ ቦታ ቢለዋወጡ ስራቸው ተመሳሳይ ነው:: ሊብስም ይችላል:: ይሄ በቀቢፀ ተስፋ ያማረ የተኮላ አለም የሚሰጠው ፍቺ ለአንዳንድ አይነት ሰው ጆሮና ልቡና የተስማማ ነው:: ለቤላም:: ተኮላ እዚህ ገለልተኛ ቦታ ተቀምጦ ይበላል፣ ይጠጣል ደሞ ይሰራል:: አገርን በሚመለከት ጉዳይ አቋም ስለሌለው የሚክደው ሃሳብ ወይም የሚከዳው ሰው የለውም::

አሁን እንዲህ ተቀምጦ በሚዝናናበት ጠባብ፣ ገለልተኛና ያልወገነ ስፍራ ከሚስቱ ከጅማ ወርቅ ረብሻ ሲላክበት ግራ ገብቶታል:: ይሄ አይነት ነገር ግራ የሚያጋባው ተኮላን ቤላ አታውቀውም:: ይህቺ የለመዳት ደስታውን የሚፃረሩ ነገሮች ሰርገው እንዳይመጡ የካበው ድንጋይ፣ የቆለፈው በር፣ የከረቸመው መስኮት፣ የደፋው ጠፈር እንዳልሰራ የገባው የዞረበትን ተኮላ ቤላ አታውቀውም::

ይሄ የገነባው አጥር ምትሃት እንጂ ተገልሎ መኖር እንደማይችል ተኮላ አልተረዳም:: አተኩሮ እድሜ ልኩን አግሩን ወደፊት የዘረጋ አንዴ እንኩዋን መናቀፉ ይቀራል? ሰው የመሆን ባህል ነው:: ጅማወርቅን ሲያቅፋት ያቀፈው አገር መሆኑን ይረሳል:: በሰላም ወጥቶ መግባቱ በልቶ መጠንከሩ ልቡ አስኪፈርስ መሳቁ ከእሱ ብቻ የመጣ

ይመስለዋል፡፡ የባለገባቸው ቤርጎዎች በሌሎች እንደ ተገነቡ ይረሳል፡፡ በነዛ ሴቶች ማህፀን ተመጠ የጠፋው ፍሱ ከሰበታ ካሮት፣ ከአርሲ ሙዝ፣ ከሃረር ከብቶች ስጋ፣ የተጠመቀ መሆኑን ይዘነጋል፡፡ የካፌ ላቴው ወተት ከሾላ፣ ቡናው ከሊሙ መሆኑን ይስታል፡፡ ከጅማ ወርቅ ሰንደቅ አንገት ላይ ተንኩዋሎ የሚወርደው የፍቅር ላቦት ትናንት የበላቸው የደጀን ጤፍ እንጀራ ከቆዳዋ ላይ ሲያካፋ አይደለም፡፡

አንዴ ብቻ ለማንም ያልነገረው ማህበራዊ ተሳትፎ ሰርቷል፡፡ ትክክል ይሁን አይሁን አያውቅም፡፡ ወንጀል ይሁን ደግ አይገባውም፡፡ በደመነፍስ ግን አድርጎታል፡፡ የአራዳ ልጅ ነበርና ምናለ ለጮኽ ሰው ቢደርስ? 70 አመተምህረት መጀመሪያ አካበቢ አሳሾች ሲከታተሉት የነበረ አጥር ዘሎ ግቢው የገባ ሚኒሊክ የተባለ ጎረምሳ ከእስር ሲብስም ከሞት አድኗል፡፡ ለሁለት ቀናት ግቢው ደብቆታል፡፡ ይሄንን ለማንም አልነገረም፡፡ በዛን ጊዜ ወዳጁ ለነበሩት ሴቶችም ይሁን ወንዶች እንኩዋን አልነገረም፡፡ ከዛ በሁዋላ ለአራትና ለአምስት አመታት ያህል በመንገድ ላይ ረኸም ጠይም ወጣት ሲያይ ቤቱ ጠልሎ ያዳነው ልጅ እየመሰለው ይደነግጥ ነበር፡፡ ስለዛ ዘመን ሲወራ ስለዚህ ልጅ ያስባዋል፡ *በህይወት ይኖር ይሆን?* አብሮት እቤት ለቆየ ጊዜ ይሰሙት የነበረውን የእሚሆይ ፅጌ ማርያም ገብሩ የፒያኖ ሙዚቃ ዛሬ ሲሰማ ትክክል እንደሰራ ያምናል፡፡ ተኮላ አራዳው መጋለጥ ደሞ በወሬ ላላ ብቻ እንደማይመጣ ይገባዋል፤ ሳይታወቅ በሰፈር ጨዋታ ተመስሎ መረጃ ከአፍ ወደ አቃጣሪ ጆሮ ያመልጣል፡፡ ቸል ብሎ ከተነገረ ተራ ወሬ ላይ ስንት ሞትና እስር ይቃረማል? ስለፈራ አይደለም፡፡ እንደዚህ አይነት ኮስታራ የመሰሉ ነገሮችን መርሳት ሰለሚወድ ለእሱ የሉም፡፡ ዛሬም ትናንትም ካርታው ውስጥ የተሳሉት አሱና የቅርብ ወዳጆቹ ብቻ ናቸው፡፡ አሁን አሁን ያው በሁለንተናው ሚስቱ ጅማ ወርቅ ብቻ፤ ደሞ አባቱ (ለአባቱ ለደጃዝማች ጆቴ በሳምንት ሶስት አራቴ ስልክ ሳይደውል፣ በዓይነስጋ ሳያያቸው ያሳለፋቸው አመታት ጥቂት ናቸው)፡፡

* *

--አንቺ ደሞ ምነው ቀናሽ እንዴ? ወድጄአት ነው አለ ቅር ባለው ፈገግታ

--ተው እባክህ 'ተኮላ ወደደ' ሲባል ግራ ያጋባል፡፡ ደህና ነህ ግን ለምን ሰርግ አልጠራኸኝም?

--ምን ልታደርጊ፣ ድሮ የተጋባነው አይበቃም::

--ሂሂሂ ምን እያደረክ ነው ግን? መንገድ ዳር ምነው ቆምክ?

--ሰው እየጠበቅሁ ነበር:: አልመጣም:: ለመሆኑ የእኛ ሰው ቀጠሮ የሚያከብረው መቼ ነው?

--ደክሞን ትተናል:: አሁን አንጠይቅም:: እንደውም ካከበረ ታሟል ወይ ምናምን ትላለህ ሂሂ

--ሃሃ አይ አንቺ:: ወደ የት ነሽ የእኔ እመቤት?

--ቤት እየገባሁ ነው፣ ለመሆኑ ፋሲልን አይተኸው ታውቃለህ? ወለላንስ?

--ማንንም አላገኘም:: አሁን የትዳር ሰው ሆኜ-

ሊቀጥል አልፈለገም

--ሰማሁ:: ጥሩ ነው:: ቁም ነገር ይሻላል እባክህ:: እንዴት ነው ኑሮ:: የምትሸፍራት መኪና ናት ይህቺ

--ምን በልጅነታችን ስናሾፍ ኖረን አሁን ትምህርቱ ከየት ይምጣ

--ዋናው ሰላም ነው:: የዲሞክራሲ ጊዜ ነው:: ሁሉም በአንድ ጊዜ አይሰምርም:: የግንባታ ጊዜ ነው:: ደሞ ስራ ክቡር ነው:: ማታ ማታ መማር ትችላለህ ትግስት ካለህ:: አለምን አይተህ ጨርሰሃል አንተ:: ያላየ ይይበት::

--አይ እሱን ተይው:: ደሞ አለም ታይቶ ያልቃል በይ:: የት ነሽ አሁን?

--ቤት ልገባ ነው:

--ከየት?

--ምነው ደጋገምክ የት ነሽን? ባለትዳር ነህ:: ከየትስ ብመጣ ምን አገባህ? ሂሂ

--ጎማ አስተንፍሰሽ ነው?

--ምናባቱን:: ይሄ ስድነት አይሻልህም በቃ አንተ

--ሃሃሃሃ ስልጣን አልያዝሽም? አንቺን ብጠይቅ ኖሮ ደህና ስራ ታገኚልኝ ነበር:: ደህና ሾፌር የእርዳታ ድርጅት ምናምን::

--እንግሊዘኛህ ደህና ቢሆን ጥሩ ነበር:: ቋንቋ ይፈለጋል:: እንግሊዘኛህን አሻሽል በእኔ ይሁንብህ:: አንድ የልጅነት ጉዋደኛዬ ከአሜሪካ መጥታ ድርጅት አቋቁማለች:: ፈረንጆችም አሉ:: ታዲያ በዚህ እንግሊዘኛህ ‘ና’ ሲሉህ ብትሄድስ:: ታስጠጣለህ::

--ሂሂ ምን እባክሽ በሁሉም ተበድዬአለሁ አለ ጅማወርቅ ነበረች በአእምሮው፣ አለመማሩ አልነበረም

--አይዞህ በስርአት ከሰራህ ይለወጣል ሁሉ ነገር:: ሚስትህስ?

--እስዋ ማታ ማታ እየተማረች ነው

--ጉድ ጉድ[2]:: ጥሩ ነው

--ስትመረቅ ስራ ታገኛለች ብለሽ ነው? ሁሉ ይማራል:: የማይማር የለም::

--አይ ኮሌጅ ነው የገባችው ወይስ......?

--አዎ ኮምፒተር እየተማረች ነው:: የት አውቃለሁ እንደዛ ነው

--ታዲያ አሪፍ ነዋ:: ኮምፒተር ገና አዲስ ስለሆነ ብዙ ይፈለጋል:: የሚያድግ ፊልድ[3] ነው:: አትጥፉ መገናኘት ጥሩ ነው

--አንዳንዴ ትዝ ትይኛለሽ::

--ተው አታሳስበኝ ሂሂ:: ደሞ አንዳንዴ ነው?

--ሃሃ በግራ እጁ ሊይዛት ሲል ሸሸት አለች

--ተው የትም ለማይደረስ ነገር

--ሃሃ የት ትገኚያለሽ ስልክሽ ያው ነው?

--ታውቀው የለ

--የቤተቦችሽን ነዋ:: የአንቺን ነው የጠየቀሁሽ

--እምቢ......

--አስመራ አልሄድሽም? ሬፈረንደም ሞልተሽ ነፃ ከወጣሽ በሁዋላ

--ምን ላደርግ ነው የምሄደው:: ኢ ካሳ ሱዊ ካሳ I kasa sui kasa ይላል ጣልያን:: እዚህ ነው የተወለድኩት፣ የማረጀውም እዚህ ነው:: አንተንና የመሳሰሉትን ትቼ የት ልሄድ ነው:: ሂሂ:: ልሳቅ እንጂ:: የአዲስ ልጅ ይናፍቃል አለችና ማራኪ ሳቋን ለቀቀች:: እንደ መደነስ እንደ አስክስታ አውራጅ ሁለመናዋን ነቀነቀች::

--አይ ቤላ ሁሌ ደስተኛ

--አንተን የሚስተካከልህ አለ እንዴ? ቆይ፣ ያቺ ማን ናት የዛ ገጣሚ ነው ሰአሊ ምናምን ጓደኛ ሮማንን መቼ ዕለት አግኝቼአት *ተከላ ሰው ሰላም ማለት አቆመ እንዴ? ምን ነካው? በግድ ለምኜ ሰላም አልኩት* አለችኝ:: ምን ነካህ?

--ዝም ብላ ነው:: የልጅ ነገር:: ስለአንቺ እንደ ጠየቅሁዋት አልነገረችሽም?

--ብትጠይቀኝ ኖሮ ትነግረኝ ነበር:: አትደልለኝ:: ምን አለችህ?

--*በቅርብ አላገኘሁዋትም ግን ደህና ናት አለችኝ::*

--እሷ ደልቷታል በል አልቁም፣ ልሂድ

ጉንጭዋን ሊስማት ፊቱን ወደ ፊቷ በቀስታ ሲሰድ ዞር አለች:: በእጁ የደረሰበትን መቀመጫዋን ጠፋት

--ምናባቱን!

[2] Good Good(ጥሩ ጥሩ)

[3] Field(የሙያ መስክ ለማለት)

እየሳቀች ትታው ሄደች። መንገድ ስትሻገር ለሰላምታ እጅዋን አነሳችለት።

ተኮላ መደፍ ላይ የቤላ ለምለም መቀመጫ ትዝታ አለ። አልተለወጠችም። እሱ ትዳር ብሎ ገብቶ አሁን በጭንቀት መወ´ጠሩ፣ መበ´ደሉ፣ መበ´ለጡ፣ ሆኖ ያህል ተሰማው። መኪና ውስጥ ገባና ጋለል ብሎ ወንበር ተደግፎ ሲያስብ ቆየ። *ጎደለብኝ ወይስ ለዚህች አለም ጎደልኩባት?*

* *

የአጥሩን በር አልፎ ግቢው ውስጥ ቆመና ያደገበትንና የሚያረጅበትን ቤት ቆሞ እንደ ሰው ላይና ታች አየው። ግራና ቀኝ ያሉት መስኮቶች አልተዘጉም። ቢጫ ብርሃን ጨለማ ውስጥ ተከርክሞ ይበራል። ግቢው ውስጥ ከበቀሉት አበቦችና አረንጉዋዴነት ከማይለቀው ግቢው የሚነሳው መአዛ በሳንባ ብቻ ሳይሆን ልብስ ዘልቆ በቆዳም ላይ ይሰማል። በስተቀኝ ካለው ቤት ቡና እውጭ ሲወቀጥ ይሰማል። *በዚህ ሰአት ቡና ሊጠጡ?* በስተግራ ካለው የአቶ ዮሐንስ ወላይሶ[4] ቤት የጃዝ ሙዚቃ ይሰማል።

[4] በ1985 አም ላይ የፀዳል ጋዜጣ (ቅፅ 3 4) የባሕል አምድ ለዮሐንስ ወላይሶ (ወዳጆቹ ስሙን አሳጥረው ሲጠሩት 'ዮሐንስ ወላ' ይሉታል) ያቀረበለት ጥያቄና እሱ የሰጠው መልስ በመጠኑ የሰውዬውን ግለ ታሪክ ይነግራል።

<u>ፀዳል፡</u> እስኪ የትና መቼ እንደተወለድክ በአሁኑ ጊዜ የት ምን እንደምትሰራና የት እንደምትኖር ንገረን።

<u>ዮሐንስ</u>፡ የተወለድኩት አዲሰአባ ከተማ ዛሬ ነፋስ ስልክ የሚባለው አካባቢ ነው። የተወለድኩበት ቦታ ላይ ዛሬ አንድ ሳተርን የተባለ ቆንጆ ሆቴል ተሰርቷል። ዕድሜዬ አስራ ሁለት አካባቢ ሲሆን ወደ ኡራኤል አዲስ ቤት ሰርተን ሄድን። ሶስት ታናሽ እህቶች አሉኝ። እናቴ ከሁለት አመት በፊት፣ አባቴ ከአመት በፊት ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል። አባቴ አንበሳ ኢንሹራንስ የሚባል ድርጅት ውስጥ የሂሳብ ሰራተኛ ነበር። እናቴ ደሞ የቤት እመቤት ነበረች። ዕድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ እንደባህሉ ቄስ ትምህርትቤት ገባሁ። መንቀልቀል አበዛ ነበርና ብዙ አለንጋ ቀምሼለሁ። በመማረር ቄሱ ላይ ድንጋይ ስለወረወርኩ እዛ እንዳልማር ተደረኩ፤ በዛሬ አማርኛ 'ገደብ ተጣለብኝ'። ቄሱ የእናቴ ንስሐ አባት ስለነበሩ በዚህ ሰበብ እናቴ ለአመታት አኩርፋኛለች። ዩንቨርሲቲ ገብቼ ቋንቋና ፖለቲካል ሳይንስ አጠናሁ። ያኔ ቀሐሥ ነበር የሚባለው። ለከፍተኛ ትምህርት እንግሊዝ አገር ሄጄ አንትሮፖሎጂና ሊንጉስቲክስ፣ ከዛ ቀጥሎ ሁለተኛ ማስተርስ ዲግሪዬን ከአዮዋ ራይተርስ ወርክ ሾፕ አግኝቼአለሁ። እዚህ እያለሁ የተዋወቅሁዋቸው እንደ ኮራጎሳን ቦይል አይነት ጎበዝ ደራሲዎች ነበሩ። ትዝ ይለኛል Water music የተባለ ልብወለዱን የመጀመሪያ ድራፍት ሲፅፍ ስለ አሰራሩ አንዳንድ ነገር ያወራኝ ነበር። እንደውም አንዳንድ አጫጭር ታሪኮቼ ውስጥ የሰፈራችን አለቃ ገብረሃና የምንላቸው ደጃዝማች ጆቴ ('የተኮላ አባት' የምንላቸው) የሰሩትን ኩሸት እየነገርኩት አንዳንድ ነገር ሊያስገባቸው ቃል ገብቶልኝ ነበር። አብዮት ሲጀመር እዚህ ዩንቨርሲቲ መጨረሻ አመት ላይ ነበርኩ። ሁሉ ነገር ከተረጋጋ በሁዋላ አገሬ ተመለስኩ። የተማርኩትና የማስተምረው ፎሬይን ላንጉጅስ ነው። እንግሊዘኛ ማለት ነው። በራሴ ልፋት ፈረንሳይኛ፣ ግዕዝ፣ አረብኛ፡ ጣሊያንኛ፣ ጀርመንኛ፣ ኦሮምኛና ጉራጊኛ እችላለሁ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጅማ ግራጁዋት ስኩል አስተማሪ ነበርኩ። ጡረታ ከወጣሁ አንድ አመት ይሆነኛል። አሁን የምኖረው አዲስ አበባ ኡራኤል እናትና አባቴ የሰሩት ቤት ውስጥ ነው። በጅማ ከተማ ላሉ ብዙ የንባብ ቤቶች በተመቸኝ ጊዜ እየተገኘሁ ስለስነፅሁፍ እወያያለሁ። ሶስት ስርአቶች ያየሁ ሰው በመሆኔ፣

‘*በዚህ ዘመን እንደዚህ ሽማግሌ የደላው የለም*’:: አቶ በዛፍና በአጥር ያለተጋረደው ኩርማን ዮሐንስ ቤት ላይ ሲያፈጥ ቆየ:: በልቡናው ዮሐንስ ግቢ ውስጥ በጎረምሳነቱ ዮሐንስ ጊታር በረንዳ ላይ ይጫወታል:: ለቀይ ቀጫጫ አጭር ቁመናው የሚተልቅ አኩስቲክ ጊታር:: *ቀኑ ደስ አይልም?* ንግግር ሲጀምር እንዲህ ነበር ዮሐንስ፡ *ቀኑ ደስ አይልም?* ይደብረው ነበር:: አይኖቹን ከዮሐንስ ቤት መልሶ እጆቹን ሱሪ ኪሱ ከቶ እንደ ሐውልት ቆሞ ሲያዛጋ ከዮሐንስ ቤት አጥር ዘልቆ የሚሰሙ ሁለት የጃዝ ዘፋኞች ፈረንጅኛቸውን አንጎራጉረው ጨረሱ:: ተሰላችቶ በር አንኳኩቶ ሲገባ ጅማዉርቅ ሳሎን አልነበረችም:: ቤታቸው በአምስት ደቃቃ ክፍሎች የተሸንሸነች ናት:: የፊት በር ሲከፈት የትም ክፍል ሆኖ ይሰማል:: ከአከፋፈቱ እሱ መሆኑን አውቃ ጅማወርቅ ከማድ ቤት ጮክ ብላ ተናገረች፡

--ምነው ቆየህ?»

ሳይመልስላት ሶፋ ላይ ከቁሙ ዘፍ ብሎ ተቀመጠ::

……እየተፍነከነከች፣ የነድ ቀለም ያለው እንደ ሜላት የሚፈስ ውስጥ ልብስዋን እንደ ተጨማደደባት ሁሉ በጣቶቿ እያመቻቸች ወደ ተቀመጠበት መጣች:: እቤት ስትሆን ሁልጊዜ በዚህ አይነት ውስጥ ልብስ ናት::

ልብስ ራሱን ባይሆንም ተመሳሳይ ቀለም ያለውን የጫጉላቸው ዕለት ለብሳ ነበር:: ያኔ የውስጥ ልብስ ለብሳ፣ በእርጅና የደበዘዘ ጥቁር ሶፋ ላይ ተጋድማ፣ የተሰራ ፀጉርዋ ተንዶ ፊቷ ላይ እንደ ጅረት እየፈሰሰ……ግራ እግሯ የተጋለጠ ቀኝ ጭንዋ ላይ ነው……ተኮላ ገና ከመታጠቢያ ቤት ወጥቶ ከወገቡ በታች ፎጣ አገልድሞ፣ ያልተጻረቀ አሪቅ ገላው ውሃ እያንጠባጠበ ቆሞ በተመስጦ አያት:: በውበቷና

የታዘብኩት ነገር ቢኖር የወጣቶች ደራሲ ለመሆን የሚያሳዩት ጉጉትና ለውይይት ያላቸው ብቃት ከድሮው የተሻለ መሆኑ ነው:: *ፍቅር እስከ መቃብርን* የሚያክል መፅሃፍ በተፃፈበት ዘመን ለውይይት ወደ አደባባይ ያመጣው አልነበረም:: ይሄ ራሱ ሰዎች ስለራሳቸው የማወቅ ጉጉት እንዳልነበራቸው ይጠቁማል:: *ስለራሳቸው ለማወቅ ካልፈለጉ፣ ራሳቸውን አያውቁምና እንዴት ስርአቱን ለመለወጥ ሞከሩ?* የሚለው ነገር ብዙ ጊዜ መጣጥፎቼ ውስጥ የሚነሳ ፅነሰ ሃሳብ ነው:: በምወደው ሰፈሬ በኡራኤል ተመልሼ መስራት ያሰብኩት ይሄንን መመርመር ነው:: ዕድሜዬ 56 አልፎኛል:: የስድስት ልጆች አባት ነኝ::አሁን የምኖረው ብቻዬን ነው:: ልጆቼ ራሳቸውን ችለው ሄደዋል:: በለቤቴ የኡራኤል ልጅ ነበረች:: ያውም ጎረቤቴ:: የድሮ ወዳጆቼ አንዳንዶቹ ዛሬም አሉ:: ቅድም የጠቀስኩልህ በቀልዳቸውና በኩሽታቸው የአለቃ ገብረሃና እኩያ አድርጌ የምቆጥራቸው ደጃዝማች ጆቴ ጎረቤቴ ነበሩ:: ወደ ስነፅሁፍ እንድገባ የሳቸው ቧልትና ቁም ነገር በትንሹ ሳይገፋፉኝ አልቀረም:: ደስታ እዛ ይገኛል፣ ከዛም ይሰጣል፣ እዛም ይሰራል ብዬ ሳይሆን አይቀርም:: ዛሬ እንኩዋን ታመው ተኝተው ቢዳከሙም አልጋቸው ዳር ተቀምጬ ስለ ድሮው ጊዜ እያነሳን እንጫወታለን፣ እንስቃለን::

በልጅነቷ......ደሞ እሷን በመውደዱ......ወዶም በማግባቱ......አግብቶም እንዲህ ለብቻቸው......ሁሉ ነገር ብቻ ለፍሬ መድረሱን እያሰበ፡ ወደፊት ቀጥ ብሎ የሚዘልቅ ተስፋውን፡ ማንም፡ ምንም ሳይለያያቸው እሱ እንዲህ ፎጣ እንዳገለደመ፣ እሷ ሁልጊዜ በዛ ነድ ቀለም ባለው ውስጥ ልብስ ተደጋግፈው......ብቻ ለረዥም ጊዜ እንዲኖሩ። ቀርቦ ሊነካት እንኳን አልቻለም፤ እዛው አጠገቡ ያገኘው አልጋ ጠርዝ ላይ አረፍ ብሎ ፊቱን እጆቹ መሃል ቀበረ። 'ተክዬ ምን ሆነክ? አመመህ?' ብላ ልትነካው እጅዋን ስትሰድ፣ በአይነስጋው የሚያየው እንደ ደከመው ድመት የሚሳበው የሚያምር ሁለመናዋ በዛ አስተዛዛኝ ድምፅ ሲታጀብ፣ ልቡ ሊቋቋመው የማይችል ኪነት ሆነበት። አለቀሰ። ጅማሮርቅ ብቻ ናት ሲያለቅስ ያየችው። በዚህ ትዝታ ሰበብ ሌላ አይነት ቀለም ያለው የውስጥ ልብስ እንድትለብስ አይፈልግም......

* *

እንደ ሜላት የሚፈስ ውስጥ ልብስዋን በጣቶቿ እየዳበሰች መጣች። እንዳስለመደችውና እንደለመደችው ጎንበስ ብላ ገና አንገቱን ስታቅፈው የቢራ ጠረን ሸተታት። ፊቷን ነጥቃ፡

--ለምን ጠጣህ?» አለችው። ደቃቃ ግን የምር ቁጣ አለ ድምፅዋ ውስጥ።

ስሜቱን በሚነካው፣ ከሚወዳት ጋር እንዳለ ሁልጊዜ ምልክት የሚሰጠውን የውስጥ ልብሷን ሲያይ ከመንታ ሰአታት በፊት ያሳለፈው ወጣ ገባ ክፉ ቲያትር ሆነበት። ይሄ ቤቱ፣ እየሳቀ ቡና የሚጠጣባት፣ እሷን ጠርቶ እየዳበሰና እየሳመ ቦታ ሳይመርጥ እዚህና እዚያ ሩካቤ የሚያደርግበት ቦታ ሳይሆን፣ የብሄራዊ ቲያትር መድረክ መሰለው። ቢበጠርም ባይበጠርም እያብረቀረቀ አናቷ ላይ ተመሳቅሎ የተቀመጠው ፀጉሯ፣ ስስ ልብሷ ስር ደረቷን ሞልተው የያዙት ጡቶቿ፣ ከሩቅ ቦታ ቦረና ነገሌ ምናምን እንደሚደወል ስልክ መልዕክታቸው በስታቲክ የተሞላ ነበር። አገጭዋን በቦክስ ሊላት ፈለገ።

የኡራኤልንና የካዛንቺስን ተንኮል የሸመደደ ተኮላ በዚህች በዚህች አይነት የተጠጣች ትሪክ እንደማይበለጥ ያውቃል። እንደሳመችው ጎትቶ አቅፎ ያልሳማት ቢራ በመጎንጨቱ ስላፈረ መስሏት፣ በለሰለሰ በሚያባባ አንደበት፡

--ለምን ጠጣህ? አለችው ደገመችና።

--አለቃዬ አስገደደኝ

--አልጠጣም አትልም

--አለቃ አላስቀይምም

--እሺ ሌላ ጊዜ ንገረው ግን.......ቆየህ ከመጣህ?

--ትንሽ ልንሸራሸር ብዬ ወደ ላይ ወጣሁ

--የት ወክ[4] ይደረጋል እዚህ አለች:: ሶፋው መደገፊያ ላይ እየተቀመጠች:: ግራ እጇ ትከሻው ላይ ነው::

--አንቺ ኮሌጅ ጨርሰሽ፣ አዲስ ቤት ላፍቶ አካባቢ እስክንሰራ እዚችው የኡራኤል ጠበል ጠዲቅ እየጠጣን አንጠብቃለን

አባባሉ ግራ እንዳጋባት አይነት አየችውና፡

--ዋናው ጤንነት ነው:: ቤት አያሳስብም፣ ኮትህን ለብሼ ዛፍ ስር አድራለሁ አለችው

--ሃሃሃሃ! ዛሬ እንዴት ቆየሽ? አላት:: ሲስቅ፣ ማላገጥ የመሰለ ቅላፄ አለው:: ስካርም መሰላት::

--አልቆየሁም፣ ትምህርት እንዳለቀ መጣሁ

*ምን አጠያየቀኝ?* ከዋናው እቅዱ የወጣና መስመር የሳተ መሰለው: : ጠይቋት ያውቃል? ስለመዘግየትና ስለመሳሰለ?

--አንድ የክፍሌ ልጅ መኪና አግኝታ ሸኘችኝ አለችው

እሱ አፍ አውጥቶ አይንገራት እንጂ ቀናተኛ እንደሆነ ታውቃለች:: ልብ አይበለው እንጂ፣ ወይም 'አራዳ ነኝ' እንደገናም 'ሴት አትሸውደኝም' ስለሚል፣ ኩራቱ አላናገረውም ወይ ገልጦ እንዲነግራት አልተገፋፋም እንጂ፣ ሰዎች መሃል አይኖቿ የሚያዩትን ሲሰልል ደጋግማ አጢናዋለች:: አትፈርድበትም:: በዕድሜ የሚያሳማ ያህል ይበልጣታል:: ቢሆንም ይሄን አይታ አልሸሸችውም:: ቢያረጅባትም የሚያምር ቁመና አለው፤ ቀልዱ መሬት ጠብ አይልም::

--የግሉ መኪና?

--ምን? ሴት ናት አለችው

እጁን እያሻሸ ወለል ወለል አየ:: ከዛ ሰአቱን ገላመጠና፡

--እ? ሰአት ያለፈ መስሎኛል፣ ገና ለጋ ነው አለ ለራሱ አይነት ድምፁን ዝቅ አድርጎ::

ወደ ሌላ ክፍል ስትገባ ያያታል:: በወላድነትና በእድሜ ብዛት ያልረገበ የኋላዋን ትንሽነትና ክብነት:: በውስጥ ልብሷ ላይ ዘልቆ የሚታየውን የሚጢጢ ሙታንታዋን ሰንበር፣ የባቷን አሞላል፣ አረጋገጥና ዛላዋን......ማጅራቷ ላይ የተኛው አጭር ላሁጫዋ......

--እንጀራ ይሻልሃል ፓስታ?

--ቶሎ የሚደርሰውን አምጪልኝ

ራስ ምታቱ መጣበት:: በአውራጣቱ ዓይነ ስቡን እያሻሸ እያለ በትሪ ላይ በያየይነቱ ወጥ የፈሰሰበት እንጀራና የሚጠጣ ውሃ በጠርሙስ ይዛ ተሜሉሳ ገባች: :

--ምን ሆንክ ተክዬ? አለችው ቆም ብላ::

--በራው ነዋ አላት

ምግቡን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣ ጎኑ ሄዳ ተቀመጠች:: ግራ እጅዋን አናቱ ላይ አስቀምጣ ግራጫ ለንቋሳ ፀጉሩን ባተኮረ ስልት ደባበሰችው: : ቀስ ብላ ተስባ፣ አይኖቿን ጨፍና መመለጥ የጀመረ መሃል አናቱን ሳመችው::

--መድሐኒት ሳምጣልህ?

እሱ የሚያውቀው መድሐኒት ትዝ አለው:: በጎን አያት:: ገፀ-መራራነቱን ሊሰርዘው አልቻለም:: ጡቶቿ መሃል አየሁህ አላየሁህ የሚጫወት 'ተ' የመሰለ ወፍራም የብር መስቀል አለ:: ደረቷ እንዲህ ለስላሳ አይመስለውም ነበር:: የደረቷ ልስላሴ አዲስ ነገር መሰለው:: *ለምን?* ጎበጥ ብላ ግራ ጉንጬን ሳመችው:: የጠቀሰችው መድሐኒት፣ መሳምና መደባበስ ለምን እንደተያያዙ ያስባል:: እንዲህ አስቦ አያውቅም:: እንደጠረጠራት የነቃችበት መሰለው: ያ ሶፉ::

--ውሃ ጥሩ ነው አለችው እንደለመደችው እጁ ሊዳብሳት ወደ እሷ አልመጣ ቢል::

ተኮላ በሃሳቡ የሚያወጣው የሚያወርደው መድሐኒቱን ነው:: ከዚህ ሃሳብ ስር ቁጣው ይንተከተካል:: ፍሙና ጢሱ አንጀቱና ጭንቅላቱ ውስጥ ይሰማዋል:: በቀኝ እጁ ፀጉርዋን እየጎተተ ከተቀመጠበት ተነሳ::

--እንዴ ፀጉሬን ነጩኸኝ!

አፏ ላይ ጥርስና ጢም አደባልቆ ሳማት::

--እንዴ ነከስከኝ!

በሁለት እጆቹ አቅፎ ተሸክሞ አነሳት::

--ውይ

እንጀራ በተዘረጋበት ትሪ ላይ፣ በጠባቡ የክፍል መተላለፊያ ተሸክሞ ወስዶ አልጋ ላይ ከቁሙ ጣላት::

--ውይ! እንዴ?! አልጋውን......!

ከውስጥ ወሰን ማለፍ እንደ ጀመረ፣ ዕቅዱን ሊንደው እንደሆነ ተሰማው:: አልጋ ላይ ገፋ አደረጋትና እንደ ደከመው ወይም እንደታመመ ሁሉ፣ ጎንዋ ወደቀ:: ያኔ ወኑ እግር በእግር ጫማውን አወለቀና ጀርባውን አዙሮ ተኛ::

ማታለል እንጂ መታለል አለመደም::

ግራ ተጋብታ፣ ልታቅፈው የዘረጋቻቸውን እጆቿን መለሰችና ጠበቀችው:: ራስዋን ትጠይቃለች: ምን

*ሆነ?* ግንባርዋ መስመር በመስመር ነው……አንድ ሁለት ሶስት……ተጠግታ ትከሻውን በእጅዋ እየገፋች፣ እየነቀነቀች ዝቅ ባለ ድምፅ እያቆላማጠች ብትጠራው እንዳልሰማት ሆነ።

--ልብስህን አውልቅና እንተኛ፤ እንጀራውንም ላንሳው ሰክረህ ነው አይደል?

አይኖቹን ሳይጨፍን ባዶ ግድግዳ ያነባል። ከእሱ ትይዩ የእሷና የእሱ ጎን ለጎን ተቀምጠው የተነሱት ፎቶ አለ። በእንጨት የተቀፈፈ ወረቀት መሰለው። ከአልጋ ተነስታ ቤት ስታዘገጃጅ፣ ልብሱን በፍጥነት አወለቀ። ራቁቱን አልጋ ውስጥ እንደገባ ተመልሳ መጣች።

--ተሻለህ አሁን?

--እም

--አትጠጣ

--እም

--አሰኘሽኝ

--እም

አልጋ ዳር ተቀመጠችና ጠበቀችው። ሳታየው ለራሱ ፈገግ አለና እንቅልፍ እንዲወስደው አይኖቹን ጨፈነ።

* *

እኩለ ሌሊት አካባቢ በዕንቅልፍ ልቡ የ 15 ሴኮንዶች አርዝመት ያለው ፈስ አንዛረረ። በድንጋጤ አይኖቹን ገለጠና ጨለማ ውስጥ አፈጠጠ። በእንቅልፍ ልቧ ጅማወርቅ ተንጠራርታ ወደ እሱ ዞራ ቀኝ እግርዋን ወገቡ ላይ እየጫነች ሳለች ነቃች።

--ምነው ተክዬ ሆድህን አሞሃል? ብላ ለማናፈስ ብርድልብሱን ገፈፈችና ጀርባዋን ሰጠችው።

ለእሱ የተረፈውን ብርድልብስ ተከናነበና በጥሞና አሸተተ። ምንም ግማት የለም።

--አይሸትም ባክሽ አለ በእንቅልፋም አንደበት። ይኼ አስገርሞት ሙሉ ለሙሉ ነቃና ብርድልብሱን ከላዩ አንስቶ በጨለማ ትራስ ተደግፎ ቁጭ አለ። ምንም አይነት መጥፎ ጠረን ወደ አፍንጫው አይመጣም። የለመደው የሚያውቀው የመኝታ ቤቱ ጠረን፣ የጅማወርቅ ሽቶና የአንሶላው ሳሙና ነው

--ይሄ የተለየ ጠረን ነው። አይሄድም እንዴ? አለች እንደ መማረር፣ ፊቷንም ወደ እሱ ሳታዞር

ከአልጋ በቀስታ እየተጎተተች ተነሳችና መብራት ሳታበራ በዳበሳ ሄዳ መስኮት ከፈተች

ተኮላ ምንም አልተናገረም፡፡ ጨረቃ ያነጣው የሰማይ መደብ ላይ ቸብቸቦዋን ያያል፡፡ ለራሱ ቃል ባይገባ ኖሮ አሁኑኑ ተነስቶ ከሁዋላዋ ያቅፋት ነበር፡፡

--አይሸተኝም አለ፡፡ እየዋሸ እንደሆነ በመጠርጠር

--አፍንጫህን ተመርመር፡፡ ወይ የሆነ የበላኸው የጠጣኸው ነገር ሆድህን በጥብጦሃል፣ ምን በላህ?

--ምነው ነገር ነገር አለሽ?

--ደሞ ድምፅ የለውም አቦ፡፡ እንዲህ ሲሆን ሆድህ በጣም ታሞአል ማለት ነው፡፡

--የአንቺ በያይነቱ ወጥ ይሆናል አለ

--ተው ተክዬ፡፡ አልበላኸውም እኮ፡፡ ምግቤን ተደስተህ በልተሃል፣ ኩሌንም ተደስተህ ጠጥተሃል

--በይ ተይኝ፡፡ ጉረኛ፡፡ ያን እያደረኩማ የማልለው የለም፡፡

ዞር ብላ በጨለማ አየችው፡፡ እንደተቆጣች ይታወቀዋል፡፡

--ካልተኛሽ እተኛለሁ አለና ብርድልብሱን ተከናንቦ ፊቱን አዞረ፡፡ ቀዝቃዛ አየር ወደ ክፍሉ ሲገባ ይሰማዋል፡፡ *ዝጊው* ሊል አስቦ ንጭንጭዋን ሊቀስቀስ አልፈለገም፡፡ ከውስጥ ተነፈሰ፡፡ እንደ *ምን ላድርግ?* አይነት፡፡

*    *

......ተኮላ ጅማ ወርቅን መሰለል ካጧጧፈ ሁለት ሳምንቶች ሆኖታል፡፡ የገረመው ለአስራ አምስት ቀን ሲሰልላት ያን ሰውዬ ደግሞ አለማየቱ ነው፡፡ መልሱ አልከበደውም፡፡ ሲያያት አይተዋለች ማለት ነው......

......መኪናው ውስጥ እንደተቀመጠ በግራ በኩል መንገዱን ተሻግሮ ወደ ዘ ድሬክ አቅጣጫ በቀስታ የሚሳብ የለቀስተኛ ሰልፍ አየ፡፡ ከሰልፉ እርዝመት ይልቅ የገረመው ጨርቅ ያልለበሰው የሬሳ ሳጥን ነው፡፡ *ይሄ ሁሉ ሕዝብ ከሳጥኑ ላይ የሚጣል ጨርቅ ያጣል?* ዛላቸው የሚስቱን የሚመስል መንታ የመሰሉ ሴቶች ነጠላ ዘቅዝቀው ያመለጣቸውን የለቀስተኛ ሰልፍ ሊቀላቀሉ ሲሮጡ አየ፡፡ ዘርፋፋ ቀሚሳቸው እየተነሳ የሚያምሩ ባቶቻቸው ይታያሉ፡፡ በእሱ የገላ ጀግራፊ የቅናት ምንጩ ሆድ ውስጥ ሆኖ ሳለ ለምን ራሱን እንደሚያመው ይገርመዋል፡፡ ለቀስተኛውንና ሬሳ ሳጥኑን ሲያይ ያለማወላወል የጅማወርቅን መሞት ተመኘ፡፡

ጅማ ወርቅን ስለእዛን ዕለት ማታው ገጠመኙ መጠየቅ የመዋረድ፣ በራስ ያለመተማመን ምልክት መሰለው፡፡ ለእሱ ይሄ አዲስ ነገር ነው፡፡ *ስትተቃቀፊ*

*አየሁሽ፣ ከማን ጋር ነበርሽ?* ብሎ ለመጠየቅ መበለጡን የጠረጠረ፣ ሲጠራጠርም የኖረ የሚያስመስለው መሰለው:: ተኮላ የሳተው ግን እድሜ ልኩን ፈሪ አንደ ነበር ነው:: ፍርሃት ለምን ያሳፍረዋል? በቻርለስ ዳርዊን ስርአት የዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብ ፈርቶ የማምለጥ ድርጊት የአንድን እንስሳ ዝርያ ከመጥፋት ያድነዋል:: የሰው ልጆች ገና ሲጀመር ከኢትየጵያ ምድር ወደ ሌሎች የአለማት ክፍል ሄዱ ከተባለ የመፍራት ቃል ፈጣሪዎች እነሱ ናቸው:: የእንግሊዘኛው *ፊር* (fear) ጀርመን ግህፋር (gefahr) ውልደቱ እዚህ መሆን አለበት:: በዚህች ስቃይና ሞት ለመፍጠር በምትለፋ ምድር ላይ (ያውም ሳይቸግራት)፣ መንቦቅቦቅ አስገራሚ አይደለም:: ያን አልተገነዘበም:: ቢገነዘብ ብቻውን አንዳልሆነ ያውቅ ነበር:: ተኮላ ደሞ መገንዘብ የሸሸው የመንጋው ጎልማሳ ናውና የማይረባ አመለካከቱን ብዙ ሰው ካዳነቀለት የማይሆነው የለም:: የሴቶችን ቆዳ እየነካ አድራሻውን የሚያጠፋው ሳይቀደም ለመቅደም እንደሆነ ለራሱም ተስቶታል:: የሚፈራው ገና ለገና የማያውቃቸው ወንዶች መጥተው የወደዳቸውን እንደሚቀሙት ጠርጥሮ ነው:: ከሴቶች ይሸሽ የነበረው፣ ከሌሎች ወንዶች የተለየ የሂያጅነት ቅመም በደሙ ስለሚመላለስ ሳይሆን፣ ይሄ መያያዝ ድንገት ቢፈርስ በማይገባው ብቸኝነት እንዳይደበር ነው:: ለራሱ (ለማንም ሳይነግር) ይሄን ማመን አንደማይፈልግ ያውቃል:: ጅማወርቅ ባትፈጠር ተመኘ:: ባትፈጠር እንዲህ አይፈተንም:: ባትፈጠር ተፈጥራ ሚስቱ ባትሆን ይሄ ጣጣ አያነደውም::

……በአይነሕሊናው እዛ እሬሳ ሳጥን ውስጥ ፍቅረኛው ሚስቱ ጅማወርቅ ናት:: ስትባልግ እጅ ከፍንጅ የያዛት ዕለት፣ መድፍ ውስጥ እንደ አረር ከቶ ለፋሲካ ንጋት ይተኩሳታል፤ ወይም ለእንቁጣጣሽ እንደ ድፎ ዳቦ ይደፋታል፤ ካልሆነም እሱን የከዳች ሌሊት ገላዋ አብጦ እንዲፈነዳ……ማሕፀንዋ ቆስሎ እየጮኸች፣ እየተፈራገጠች ወሲብ እየረገመች ስትሞት……

ባልገባው ምክንያት ‵ከሚስቴ አጣሁት′ የሚለው ፍፁምነት እንደቀሰቀሰው ሁሉ ሌላ ሴት ያያል:: እንዲህ ማድረግ ከጀመረ ሶስት ቀኑ ነው:: ግን ማመን አልፈለገም:: ‵ሚስቴ አታለለችኝ′ ብሎ የሚከታተል ሰላይ ባል፣ እንዲህ ማሰቡ ፍትህ የለውም ብሎ ይሆናል:: እየሮጡ የሄዱት ልጃገረዶች ያስታወሱት ሚስቱን ብቻ አልነበረም:: ወጣትነቱንም ነው:: ብቻ ጅማ ወርቅ እዛ ሬሳ ሳጥን ውስጥ እስከ አንገቷ ተገንዛ ተንጋላ ሲያስባት፣ ከዛ ጀርባ በቸልታ

በነፃ ተለቆ የሚውረገረገው የልጃገረዶቹ ዛላ እንደ ሽፍትነት ተሰፋ፣ በትክክል እንደ በቀል፣ ገላውን በሴሰን ወረረው::

የለቀስተኛው ሰልፍ ካለፈው በኋላ፣ በእጁ እያገላበጠ ይጫወትበት የነበረውን ማስታወሻውን ጋቢና ውስጥ አለቃው የሚቀመጥበት ወንበር ላይ ወረወረ:: የወረወረው ማስታወሻ መቀመጫውን እንደ ነካ ቆጣ ያለች አጭር ፈስ አመለጠችው......




ፈስ መሆኗ አሻሚ ባይሆንም፣ በባህርይዋ ወረቀት ሲቀደድ፣ ወንበር ሲንፏቀቅ፣ ማንነቷ የተምታታ፣ ከራሷ የተጣላች፣ ፈጣን፣ በግዴታ (በአደጋ ሰበብ) ብቅ ያለች ግን ቅልብጭ ያለች ናት:: ተኮላ ለአስራ አምስት ቀናት ሙሉ የለመደው ድምፅ ስለሆነ ብዙ አልተጨነቀም:: ድንገት ፈሷ ሳታስጠነቅቅ መጥታ ያስከተለችው እሷን የመሰለ ቅራቅንቦ እንዳለ በመጠርጠር፣ ዙሪያ ገባውን ተገላምጦ አተኩሮ በሃይል አማጠ:: ምንም አልወጣውም::

አካባቢውን እየፈተሸ ወደ ግራ ዞር ሲል እወዲያ መንገዱን ተሻግሮ 30 ሜትሮች ያህል እርቆ ፍራፍሬ ለመሸጥ ከተጎለተች አንዲት መልከመልካም ሴትዮ ጋር አይን ለአይን ተገጣጠሙ:: በደንብ ሳያያት በቸልታ ገርምሟት ዞር ካለ በሁዋላ በደነገጠ ፍጥነት፣ ዐይኖቹን ወደ እሷ መለሰ:: ገፁ ላይ መገረም ፈለቀ:: ፊቷን ከእሱ አዙራለች::

--አላምንም፣ ትሆን እንዴ? አለ ለራሱ

ከመኪናው ወጣና ሴትዮዋን እያየ ሲጋራ ሊለኩስ ሞከረ:: ስለልቻለ አይኖቹን ወደ ትንባሆው መልሶ የእሳቱ ቢጫ ነጥብ ውስጥ አስተካክሎ ከተተና ለኮሰ:: በጥልቅ ሳበና ጢሱን እያቦነነ ሴትዮዋ ወደ ተቀመጠችበት ሄደ:: ከጀርባዋ በኩል የሚመጣውን የሚያቃጥል የአስር ሰአት ፀሐይ እንዲጋርድላት አይነት አናቷ ላይ ነጠላዋን ጣል አደርጋለች::

ተኮላ ተጠጋና ሊያያት ሞከረ:: አልቻለም:: ፊቷን ተከትሎ ሊዞር አልፈቀደም::

--እህት አለ

ዞር አለችና አየችው

--የማውቅሽ መሰለኝ አለ ፊቱን አኮሳትሮ

--እኔን? ኸረ እንጃ እኔ እንጃ አላውቅህም

--ድሮ ቄራ ትኖሪ ነበር?

--ቄራ? ከአገር ቤት ከመጣሁ ሁለት አመቴ ነው......ጥሩ ሎሚም ቃሪያም አለኝ ከፈለክ

--አልፈልግም::

--አንድ ቄራ የማውቃትን ሴትዮ መሰልሽኝ፡ የእውነት ጠቆር አልሽ፣ ደሞ አረጀሽ እንጂ:: አልመሰችለትም ወይም ስህተቱን ተረድቶ ወሬውን ቀጠለ

--በልጅነቴ የማውቃት ልጅ ነበረች:: ሰማይ ሰማይ እያያ ሲጋራውን መጠጠ

--ሰላሳ አመት ያልፋል:: ቆንጆ ልጅ ነበረች:: ጢሱን ተፋ

እወዲያ የለቀስተኛውን ሰልፍ እያየ አሁንም በከፊል ልቡ፣ ባልተሸፈነው የሬሳ ሳጥን ይገረማል:: ሴትዮዋ ትኩረቱ ወደ ሌላ እንደዞረ ስታይ በፍጥነት ከላይ እስከ ታች ገረመመችውና ፊቷን ቶሎ መለሰች::

--ድሮ ጥሩ ጊዜ ነበር አለ የምትሰማው መስለው

--ሎሚ ትገዛለህ? አለች በቁናዋ የያዘቻቸውን ፍራፍሬዎች እየነካካች፣ በከፊል መሬት በከፊል እግሮቹን እያየች

--ምን ላደርገው? አለ

ልቡ ሬሳ ሳጥኑ ጋ ቢሆንም ዓይኖቹ መንገድ ዳር ወደ አቆመው መኪናው ያያሉ:: አንድ ነጭ ውሻ እየሮጠ መጥቶ ቆመና ቀጠሮ እንዳለው ሁሉ እግሩን አንስቶ ሁዋላ ጎማው ላይ መሽናት ጀመረ:: እዚህ መጥቶ ሊሽና ያቀደ ይመስላል

--ምናባቱን ይሄ ውሻ በአገሩ ስልክ እንጨት ጠፋ አሉት?! ዞር በል!

ውሻው እየሸና ቀና ብሎ ተኮላን አየውና መሽናቱን ቀጠለ:: የሚብለጨለጭ ውሃ ከጎማው ላይ ይወርዳል:: ተኮላ ከሲጋራው መጠጠና ሴትዮዋን ትቷት ወደ መኪናው ተመለሰ:: ከመድረሱ በፊት ውሻው መሽናቱን ጨርሶ ሽሽት ብሎ ቆመ::

ተኮላ በመገረም አየውና፡

--ምን ፈለክ አሁን? ብሎ ድንጋይ ሊያሳ አጎነበሰ:: ውሻው እንደ ፈራ ሁሉ ሽሽት አለና የትም ሳይሄድ ቆመ:: ተኮላ ጠጠር ለቅሞ ቀና ሲል ውሻውን እዛው ቆሞ አየው:: አስተያየቱን አልወደደውም:: ከእሱ የሆነ ነገር የሚጠብቅ ይመስላል:: መመታት? ተኮላ ድንጋይ ወረወረ:: ውሻው ዞር ብሎ ድንጋዩን አሳለፈና ቦታውን ኢንች ሳይለውጥ ቆመ:: ፀጉሩ እንደ በረዶ የነጣ ነው:: አንገቱ ላይ አረንጉዋዴ ጨርቅና ከቆዳ የተሰራ የመሰለ ቡላ ማተብ ነገር አለው:: እንዲህ አይነት ማተብ ያጠለቀ ውሻ አይቶ አያውቅም:: የተጠነቆለበት መሰለው::

--ምናባቱን ምኑ ደረቅ ነው:: በመኪናዬ እንዳልወጣብህ፣ ጥፋ! አለና ወደ ሁዋላው ወደ ሴትዮዋ ወደ ተቀመጠችበት ዞር አለ:: ስታየው እንደ ነበረች ሁሉ ፊቷን ቶሎ ወደ ሻገር ሆቴል ዞር አደረገች:: *ስሚ ማን ነበር?*

ከ30 አመታት በሁዋላ እሷ እንዴት ትዝ አለችው? እንዳሻው የሆነበት የልጅነት ዘመኑ እንደ ሰው ናፍቆት? የድሮ ዘፈን ሲሰማ፣ የአሬታ ፍራንክሊንን *ሪስፔክት*፣ የጂሚ ሄንድሪክስ *ፐርል ሄዝ*፣ የቢትልስ *ሉሲ ኢን ዘ ስካይ ዊዝ ዲያመንድስ*፣ ማርቪን ጌይ፣ የሸገኔዎችን *ኩሉን ማን ኩሉአታልን*፣ የባሪ ዋይት *ሴክሲ ቲንግን* ልቡ ያለፈውን እንደሚናፍቅ ሁሉ የሆነች ሌላ የማያውቃት ሴት የሚያውቃትን አስታውሳው? እዚህ ዙፋን ቢለዋወጥ ልጅነትን አንረሳም አይነት? የዛ ዘመን ትርፈራፊ ቢሰደብም፣ ቢናቅም ጉልምስናን በዝምታው ያጣፍጣል አይነት?

ለሁለተኛ ጊዜ ድንጋይ አነሳና በቸልታ ወደ ውሻው አቅጣጫ ወርውሮ የሴትዮዋ ነገር እያብሰለሰለው መኪናውን ተደግፎ እያሰበ ቆመ::

በጊዜ ነፋስ ተጠርጎ ዱካ እንኩዋን ያልተወው ልጅነቱን አሰበ:: ያኔ ገነት ሆቴል በውሊንግ ኩዋስ ወረውሮ ቢራውን ጠጥቶ ሞቅ ሲለው ለራሱ *ኮረፌዋ ጋ* ልሂድ ነበር የሚለው:: ቀጭን ሸንኮራ ሴት ነበረች:: ጠላ ጠላ የምትሸት:: እሱ ከላይዋ መሎቲ፣ ከሆዱና ከከንፈሮቹ በወሲብ ትኩሳት የቀለጠ የኮተሌት ወዝ እያገሳ:: ከውስጥዋ የማር ወንዝ የሚወጣ:: እንዲህ ሆኖም አብሮአት ተቀምጦ ዳቦ የቆረሰበት ጊዜ ትዝ አይለውም:: ነጠላ ከለበሰች እንኩሮ አንኩሮ ከምትሸት ልጅ ጋር የአራዳ ልጆች ቢያዩት እንዳይገሉት በነገር:: ታላቁ አማላይ ቢሆንም ታላቁ ወንድ አልነበረም:: ልቡ፣ አንጎሉና ሙርጡ በተለያየ ሶስት አቅጣጫ ሲሄዱ አልሰበሰባቸውም:: *ጅማ ጋ* እስኪደርስ::

*ስሚ ማን ነበር? ምን አስጨነቀኝ*:: ሰክሮ በየግሮሰሪ ሲዞር ነው እዛ ቤቷ ቁራ የገባው:: በስህተት:: ስህተቱ ግን ዕድሉ ነበር:: ልብሷን ስታወልቅ ከቅላቷ የተነሳ ከላይዋ የሚነሳው የጨረር መአት:: በጨለማ ወስዶ ፀሐይ ሳትወጣ ቤቷ ይመልሳታል:: ምናልባት ሚስት አድርጎ 'እንዲጠቀልላት' ጠብቃለች:: ድሮ *መጠቅለል* ለሴቶች ድል አስተኔ ነበር እንደ የ *ጠቅል አሽከር*፣ እንደ *ጠቅላይ ግዛት*፣ እንደ *ጠቅላይ አቃቤ*፣ እንደ *ጠቅላይ ሚኒስቴር* ምናምን:: ምናልባት የሚሰጣት ገንዘብ ይሆናል ከእሱ ያከረማት::

አብዮት ከመጣ በሁዋላ ገነት ሆቴል የሚሰበሰቡ ብዙዎቹ አራዶች ተበታተኑ:: ከቀሩት ጋር ድራፍት እየተጎነጩ ስራቸው ደርግን መተቸት ነበር:: እሱ አፍቃሪ እንጂ ተሳዳቢ አልነበረም:: *ሜክ ላቭ ኖት ዋር፣ የዚህ አገር ሴቶች ወንድሜ ካሽና ወዳጅ መሳይ ነው የሚፈልጉት* ማለት ጀመረ:: ለተኮላ *የሴቶቻችን ሱስ ከጦረኛና ከሃብት ነው:: የሃበሻ ሴቶች ሲቅለሰለሱ የተቀደሱ ይመስላሉ እንጂ የእጅ አዙር አጥፊዎች ናቸው:: በወንዶች መሃል የሚመላለሱ ባንዶች ናቸው::* ተኮላ እንደሚለው ወዲያ ወዲህ የሚሯሯጠው ከዚህ ደደብነታቸው ሊያድናቸው ነበር:: ሴቶች አግዜርንና ባህላቸው የሰጣቸውን የማስደሰት ሙያቸውን እንዳይረሱ ነው:: ተደብረው እንዳይደብሩ ሲያደርግ ነው:: ሴት ካላቺንኮቭ ታጥቃ ስትሄድ ሲያይ ይገረማል:: *ከምትገለው አትተኛውም? ደስታን በመግደል ነፃነት አለ?*

ታዲያ እሱ ለምን ያቆማል? ለማን ብሎ ያቆማል? ለማን ብሎ ይሸሻል?

ከመኪናው እየወጣና እየገባ፤ ወዲያ ወዲህ መንገደኛም ለቀሰተኛም እያየ፣ ሊያስበው እየፈለገ አንስቶ የሚጥለው፣ የሚሸሸውና ያራቀው ግምቱ ከአእምሮው ጀርባ ሞቆት ቁጭ ብሎአል:: ‘እንደ ልጅነቴ መዳራት፣ መጠጣትና ማጤስ አቆምኩ’ ይበል እንጂ ሽበት ማቆጥቆጥ ከጀመረ አናቱ እስከ እግሩ አውራጣት፣ በትንሹ ይሄን እምነቱን መክዳት መጀመሩ ይሰማዋል:: አንዳንዱ ከያኒ ሊሆን ነው የተፈጠረው፣ አንዳንዱ ተወዳጅ መሪ ሊሆን ነው፣ አንዳንዱዋ ብተለፋ እንኩዋን ሽርሜ ከመሆን አታመልጥም፣ አንዷ ለሐኪምነት የተፈጠረች ናት:: አንዳንዱ ጠንቋይነት ይቀናዋል:: አንዳንዱዋ እናት እንድትሆን ፈጣሪ ያለመለማት ናት:: ተኮላ ሴት አውል ነው:: ግን ሴት አውልነትን ማነው ወንጀል ያደረገው? ማሰብ እየፈለገ ከማሰብ የሚሸሸው ይሄን መሰረታዊ ነገር ነው::

ለተኮላ ጅማ ወርቅን ሚስቱ ያደረገበት ዋና ቅመሙ የሴት አውልነት ልምዱ እንደሆነ ሊዘነጋ ይጥራል:: ተፈጥሮው ከሰጠው ችሎታ ወጥቶ ሌሎች ወደ መደቡለት ሰነስርአት መመዘኛ መግባቱን ያስባል:: ሚስቱ የወደደቸው እንደ ጎረምሶቹ ችኩል በአለማለቱ አይደለ? ይሄ አለመቸኮሉ በሴት ገላ ከመሰልቸቱ የተነሳ አይደለ? ይሄ ደሞ ከሴት አውልነቱ ያገኘው ትርፍ ነው:: ጅማወርቅን ቢወዳትም በመረካከባቸው ገቢር ውስጥ የሌላ ሴት ሴትነት ትዝ ይለዋል:: ሴቶች ለተኮላ መልካቸው

ሺህ ጊዜ ቢለያይ፣ ልክ አንደ ፀባያቸው የገላቸው ሰኬትና ሴትነት በተወሰኑ የተቆጠሩ ፀባዮች የሚደነገግ ነው፡፡ በሚስቱ በኩል ብዙዎቹን ያስታውሳል፡፡ በቦታ፣ በጊዜና በማህበራዊ ቦታቸው ቢራራቁም በትውስታ ታሪኩ ሁሉም በሆነ መልክ ጥቂት ናቸው፡፡

ከመኪናው ወጣና መንገድ ተሻግሮ ከአንድ ሱቅ ፓኬት ኒያላ ሲጋራ ገዛ፡፡ ከፊት ቀደም ሲል ያነጋገራት ሴትዮ ከነበረችበት ፈቀቅ ብላ ሰው የሚተላለፍበት መንገድ ዳር ጉልቷን ደግማ ዘርግታለች፡፡ ከሁዋላዋ የሚያየው ጥቁር ዣንጥላና ከዝተት ጨርቅ መሃል ብቅ ያለ ቅርፁ የሚያምር ባት ነው፡፡ ሴትዮዋን ከፊት ለፊት ለማየት አስቦ አንድ ሁለቴ እንደተራመደ ሌላ ሲጋራ መለኮስ አማረው፡፡ ቀና ሲል ከእሱ ራቅ ብሎ የካኪ ካፖርት ለብሶ የቆመ አንድ ፀጉሩን የተላጨ የሆቴል አስተናጋጅ አየ፡፡ ሴትዮዋን ችላ ብሎ አለፋትና ወደ ልጁ ቀርቦ በአናቱ ሰላምታ ሰጠው፡፡

አስተናጋጁ ምንም ሳይናገር አንገቱን ብቻ ሰበር አድርጎ ሰላምታውን መለሰለት፡፡

--ስማ ቺፍ አልጋ ስንት ነው እዚህ የምታከራዩት?

--ሃያ ብር

ሲጋራውን ከፓኮው ሊያወጣ በጣቶቹ እየተሟገተ፡

--ደህና ነው ክፍሉ?

--ጥሩ ነው፡፡ እዚህ አካባቢ ያለው ደህና ሆቴል ይሄ ነው፡፡ እነዛ ሳይጠሩ አለ ወደ ድሬክ ካፌና ሳተርን በአገጩ እያሳየው

--ሰማህ ሰማህ ደበሌ! አንዲት ሴት ከሩቅ ጠራቸው፡፡ ልጁ ፊቱን ወደ እሷ አዞረ፡፡

--ይሄን የእጅ ሰአት አርባ ልግዛው?!! አለችው

--ያሰርሽው ምን ሆነብሽ ትጊ?!

--ውሃ ገባበት!

--ሰላሳ ግዢው፣ ስማ አንተ ሰላሳ ሽጥ! አለ 'ደበሌ' የተባለው ወደ ሰአት አዙዋሪው ጎረምሳ እየጮኸ

ተኮላ ሲጋራ በአፉ አስገባና ከኮት ኪሱ የክብሪት ፓኮ አወጣ፡፡ የክብሪቷን መሳቢያ በአውራጣቱ ሲገፋ ክብሪት እንደጨረሰ አየ፡፡ *ክብሪት አለህ?* አይነት ደበሌ የተባለውን ልጅ በእጅ ጥቅሻ ጠየቀው፡፡ ልጁ በአሉታ ራሱን ነቀነቀ፡፡ ተኮላ አሻግሮ ሆቴሉ በረንዳ ላይ የተቀመጡ ሰዎችን በአይኑ ሰለለና የሚጤስ ነገር ሲያይ ወደዛ በቀስታ እየተራመደ ሄደ፡፡ የሻገር ሆቴል በረንዳ በእንጨት ሪጋዎች የታጠረ ሰፊና የመኖሪያ ቤት የመሰለ ነው፡፡ ከፍታው የመሃከለኛ ሰው ቁመት ወገብ ይደርሳል፡፡ ተኮላ በደረጃው ከመውጣት ይልቅ



t.me/BookandYou

ከውጭ ቆሞ የሲጋራ ጢስ ከየት እንደሚመጣ አየና ጣቱን አጮኸ:: የጨርቅ ቆብ በግራ እጁ፣ ሲጋራውን በቀኝ እጁ የያዘዘ አንድ ጎልማሳ ምን እንደሚፈልግ በአይኖቹ ጠየቀው:: ተኮላ በአፉ ሰክቶ ወደያዘው ያልተለኮሰ ሲጋራ አሳየው:: ሰውዬው የሚያጤሰውን በዝምታ አቀበለውና በባርኔጣው ፊቱን አራገበ:: ያኔውኑ ትጊ የተባለችው ሴት እየሳቀች መጥታ ሰውዬው ጭን ላይ ተቀመጠች:: ተኮላ የተዋሰውን ሲጋራ መለሰና ለሰውዬው በአንገቱ ንቅናቄ ምስጋና ሰጥቶ ወደ መኪናው መሄድ ጀመረ:: ባለባርኔጣው ምስጋናውን የሰማ አይመስልም::

መሃል መንገድ እንደደረሰ የረሳው ነገር ትዝ እንዳለው ሁሉ ወደ ለቀስተኛው ሰልፍ ዞር ብሎ አየ። ሰልፉ ቆሟል ወይም አንድ ነገር ሆኗል። የጓጎለ ምጥን ሽሮ መስሎ ከሰዎች አናት ላይ የሚንሳፈፈው ሳጥን ወዲያና ወዲህ ይላል። ሊወድቅ ይመስላል። ተኮላ ግራና ቀኝ እያየ፣ ሲጋራውን እየሳበ መንገዱን ተሻገረና የመኪናውን አፍንጫ እንደደከመው ሁሉ ተደገፈ። አይኖቹ ሩቅ ያያሉ። ከለቀስተኛው ወዲያ መንገድ ሊሰሩ የተመደቡ ትራክተሮች ግንቦት ፀሐይ ስር የተመደበላቸውን ብረታም አንቅልፋቸውን ይለጥጣሉ። የሚቆሙበትን ቦታ ሲለዋውጡ እንጂ ሲሰሩ አላያቸውም::. ከወዲያ በኩል ሸገር ሆቴል በረንዳ ላይ ጠና ያለችዋን ዕድሜዋ በግምት ሃምሳ የደረሰ፣ ቀልቀል የሚያደረጋትን ሰአት ገዢዋን ሴትዮ ያያል፡ ፡

የሚጤሰውን የራሱን ትንባሆ ያያል:: የሃያ ብር አልቤርጎውን ያያል። የከዳችው ባለጌ ሚስቱ ወይም ልትከዳው ወዲያ ወዲህ የምትል ሚስቱ የቀዘቀዘ ጠይምነቷ እዛ ጨለማ ሳጥን ውስጥ በጀርባው ተኝቶ ያስባል……

መኪናው ጋቢና ገብቶ መስኮት ከፍቶ ሲጋራውን ለመጨረሻ መጥጦ ጣለና ግንባሩን መሪ ላይ አስደግፎ ዓይኖቹን ጨፍኖ የሚያንቀላፋ ወይም የሚያስብ መሰለ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ቀና አለ። ሌላ ሲጋራ ለመለኮስ የኮቱን ኪስ ሲዳብስ፣ በእሱ እድሜ ክልል ያለች ጥቁር በጥቁር የለበሰች ደርባባ ሴት፣ ከለቀስተኛው አጀብ ተነጥላ፣ ከ ዘ ድሬክ ሬስቶራንት አጥር አጠገብ መንገድ ዳር ሱቆች ፊት ለፊት ስትቀመጥ አየ:: ሊያነጋግራት ፈለገ:: መኪናውን አስነስቶ ትንሽ ነዳና ፊት ለፊቷ ወስዶ አቆመው:: በእሱና በሴትዮዋ መሃል በድንጋይ፣ በተሰባበረ ጠርሙስ፣ በተቀዳደደ ጨርቃ ጨርቅ፣ በተከተረ ቆሻሻ ውሃና በተቀዳደደ ፌስታል መሞላት የጀመረ ጠባብ ቦይ አለ:: ከመኪናው ወጣና እጆቹን ሱሪ

ኪሶቹ ከቶ ወዲያ ወዲህ እያለ ሁለመናዋን አጠና፡፡ ያዘነች ሳይሆን የተበሳጨች መሰለችው፡፡ *ምን ያበሳጫታል?* በስተግራዋ ከእሷ ብዙ ሳይርቅ ዘ ድሬክ ካፌ በረንዳ ላይ ብዙ ሰዎች ለስላሳና ጁስ ይጠጣሉ፡፡ ያወራሉ ይስቃሉ፡፡ ሴትዮዋ ከዕንቅልፏ እንደነቃች ሁሉ የተኮሳተረ ፊቷን ዳብሳና አፍዋን አጣጥማ ቀሚሷን ለማስተካከል ከወደ ጉልበቷ ከፍ አድርጋ ወደፊት ስትስበው፣ ተኮላ በውልብታ ነድ ቀለም ያለው ውስጥ ልብስና የጭኖችዋን ማራኪ እርዝመት አየ፡፡

ሳሉን ሳለና ቦዩንም ሳይሻገር፡

--ጤና ይስጥልኝ! አለ ለሴትዮዋ

ቀና ብላ ሰላምታውን ሳትመልስ ግራ በመጋባት አየችው፡፡

--ደህና ነሽ? ልርዳሽ

ለማገር የፈለገች አትመስልም፡፡ በማሳቸት አይታው፣ ፊቷን ዞር አድርጋ፡

--ደህና ነኝ *ምን ትረዳኛለህ?* አለችው፡፡

የመጨረሻዎቹን ሁለት ቃላት ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ፡

ሌላም ሚስስ ሳይጠበቅ......ድሮ ድሮ እንደሚለው *ዘንካታን በዘበሬታ፣ ወትዋታን በዝምታ*......(ከአባቱ ከደጃዝማች ጆቴ ነው የቀዳው) ቦዩን ዘለለ፡፡ ቀለል ያለች ቱኒ፣ ስሟ 'ቱስክ' የሚሆን አየር ላይ እየተንሳፈፈ እያለ ለቀቀ፡

*ምናባቱን!* አለ በልቡ

ፍገግ እያለ፣ ሴትዮዋ ፊት ለፊት እጆቹን ሱሪ ኪሶቹ ከቶ ቆመ......